ትክክል አይደለም። በዚህ አንጻር ክርስቲያኖች ፍጹም ጠንቃቃ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ክርስቲያን አጋንንት ይገቡበታል የሚሉ ሰዎች፣ ትምህርታችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት የሚጠቅሷቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትና የሙግት አካሄዶች ስሑት መሆናቸውን፣ በአሰሳ መልክም እንኳ ቢሆን ለማየት ሞክረናል። ክርስቲያኖችም ምንም ዐይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ የሌለውን እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የሚያስተምረውን እስተምህሮ የሚቃረን ይህ ዐይነቱን ትምህርት ያሰምንም ማቅማማት፣ ወግድ ሊሉ ይጠበቅባቸዋል። አጋንንት፣ ሰይጣን፣ ዲያብሎስ፣ እርኵሳን መናፍስት...ያለ ሁሉ፣ የእርኩሳን መናፍስት ባላንጣ እንዲሁም የአምላክ ባለሚል ነው ብሎ ማሰብ ትክክል አይደለም።

"የዘር ማንዘርሽን መርገም ልሰበርልሽ"፣ "የቍጣ መንፈስ ላስወጣልህ"፣ "ሰይጣን ስኬት እንዳታገኚ እየተዋጋሽ እንደ ሆነ መንፈስ ቅዱስ ይናገረኛል" ወዘተ የሚሉት ንግግሮች ሁሉ፣ አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም። ቢያንስ እስካሁን በሁለት ተከታታይ ምዕራፎች ያየናቸው ነጥቦች፣ ይህን አስተሳሰብ በፍጹም እንዳንቀበል እንዲያውም አስተምህሮውን በግልጽ እንድንቃወም የሚያስገነዝቡን ናቸው።



# ክፍል ዘጠኝ

## በአባይ ነባዮችና በመናፍቃን ተዘውትረው የሚታዩ ባሕርያት የትኞቹ ናቸው?



### ሀ. የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርይ

በዚህ ክፍል ለማየት የምንሞክረው፣ በአብዛኞቹ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ዘንድ ተዘውትረው የሚታዩትን አስተምህሮአዊ ባሕርያት ነው[1]።

[1] የዚህ ክፍል መሠረታዊ የሙግት ጭብጥ በአብዛኛው የተወሰደው:— *Alan W. Gomes*, *Unmasking the Cults* *(Grand Rapids: Zondervan, 1955)* ላይ ነው።

ክፀሓይ በታች ያሉትን የተሳሳቱ ትምህርቶች ሁሉ አጥንተን ልንዘልቅ አንችልም፤ ነገር ግን የአስተምህሮአቸውን ተመሳሳይ ጠባይ ማወቅ፣ ራሳችንን ከመናፍቃን እንቅስቃሴ ለመጠበቅና በእንቅስቃሴው ውስጥ ያሉትን ሰዎች ወደ ትክክለኛው መሠረተ እምነት ለማምጣት ትልቅ ቦታ አለው።

የሐሰተኛ መምህራንን አስተምህሮአዊ ባሕርይ ስናጠና፣ ሁሉም አባይ ነባዮችና መናፍቃን ሁሉንም ባሕርያት በእኩል ደረጃ ይጋራሉ ማለት አይደለም[2]። ነገር ግን አባይ ነባይ የሆኑት ከክርስትና ትምህርትና ሥነ ምግባር ስላፈነገጡ፣ አስተምህሮውንም ፊት ለፊት ስለተቃወሙ ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች ከመሠረታዊ እምነታቸው ይልቅ፣ ለልምዳቸው ትኩረት ይሰጣሉ። እንዲሁም አንዳንድ ክርስቲያናዊ ተቋሞች፣ የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም ዘዴ ይከተላሉ። ይህ አካሄዳቸው መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት እስካልተቃረነ ድረስ እንዲሁም የክርስትናን ስም እስካላጐደፈ ድረስ ልንታገሠው እንችላለን። ምክንያቱም ሁላችንም ብንሆን በማደግ ላይ ያለን ክርስቲያኖች እንጂ፣ ዐድገን ያበቃን እንዲሁም በክርስቲያናዊው አስተምህሮ ላይ ፍጹም የሚባል ዕውቀት የተጐናጸፍን ሰዎች አይደለንም።

---

[2] መናፍቃን መሠረታዊ/ዐበይት የሚባሉ የክርስትና ትምህርቶችን አንድ ወይም ከአንድ በላይ መካድ ሲሆን፣ አባይ ነባዮች ግን መሠረታዊ የሚባሉትን ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች እናምናለን የሚሉ፣ ነገር ግን ኑፋቄን ትምህርቶችን የሚክዱ እንዲሁም ክርስትናን በሥነ ምግባራቸው እያስነቀፉ የሚገኙትን ሰዎች ነው። ለበለ ማብራሪያ፣ "የመሠረታዊ ቃላት ፍካሬና እማሬ" የሚለውን ክፍል ይመልከቱ።



# ለ. የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርያት

## 1. አስተምህሮተ ሥላሴን መካድ

ርቱዕ (ትክክለኛ) የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፣ በአንዱ የእግዚአብሔር ባሕርይ ሦስት ዘላለማዊ አካላት ይኸውም አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አሉ ብሎ ያምናል። ምናልባት ሁሉም መናፍቃን የሥላሴን አስተምህሮ ይክዳሉ ቢባል ስሕተት አይሆንም። አንዳንድ መናፍቃን የሥላሴን አስተምህሮ ከአረማውያን የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ ጋር ሲያመሳስሉት፣ አንዳንዶች ደግሞ አስተምህሮውን እንደሚቀበሉ ያውጃሉ፤ ነገር ግን አስተምህሮውን የሚያብራሩበት መንገድ ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት እጅግ የራቀ ነው።

በአንጻሩ የዘመኑ አባይ ነባዮች፣ "እግዚአብሔር ማን ነው?" የሚለው ወሳኝ ጥያቄ፣ የመናፍቃኑን ያህል ሲያሳስባቸው አይታይም። እንዲያውም ለአንዳንዶች ይህ ዐይነቱ ውይይት ጊዜ ማቃጠል ነው። ምክንያቱም ቀዳማይ ትኩረታቸው የመሠረተ እምነት ንጽሕና ሳይሆን፣ ንዋይና ዝና መሰብሰብ ነውና። በመሠረቱ ብዙ አባይ ነባዮች መሠረታዊውን የክርስትና ትምህርት በቅጡ አያውቁትም። ይህን ለማጣራት እነርሱን በቅርበት ማወቅ አያስፈልግም፤ በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን ላይ የሚለጥፉትን ስብከት ለዐሥር ደቂቃ ማዳመጥ ብቻ ከበቂ በላይ ነው። እንዲያውም አንዳንዶቹ የት ቤተ ክርስቲያን እንደ ነበሩ እንዲሁም ማን ደቀ መዝሙር አድርጎ እንዳሳደጋቸው የሚታወቅ አንዳችም ነገር የለም። ይህ ደግሞ አስተምህሮአቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሥነ ምግባራቸውም ከምርመራ እንዴት እንደ ተደበቀ የሚያሳይ ነው።

## አስረጅ

ከምሥረታው ስመን ጀምሮ እስከ አሁን፣ የሥላሴን አስተምህሮ በቀጥታ የሚቃወመው "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት ነው[3]:: እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ፣ የሥላሴ ትምህርት አረማውያን በክርስትና እምነት የጣሉት አሻራ እንደ ሆነ ይገለጻል[4]::

የሥላሴን አስተምህሮ ከሚክዱ መናፍቃዊ ድርጅቶች መኻል "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" ሌላው የሃይማኖት ተቋም ነው:: እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ አብ እውነተኛው አምላክ ሲሆን፣ ኢየሱስ ደግሞ ወልድ ወይም ልጅ ተብሎ የሚጠራው የራሱ ማንነት የሌለው አብ ላይ የተለጠፈው ሥጋ ነው:: መንፈስ ቅዱስ ደግሞ፣ የአብ ሌላው ስም ነው:: እንደ ድርጅቱ ትምህርት "ኢየሱስ ክርስቶስ"፣ "ጌታ ኢየሱስ" ማለት አብና ወልድ ማለት ነው:: ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን፣ አምላክ የተጠቀለለበት (የተሸፈነበት) ሰው/ሥጋ ነው[5]::

ሞርሞኖች የሥላሴን አስተምህሮ እንደሚያምኑ ይገልጻሉ፤ ነገር ግን ለትምህርቱ በሚያቀርቡት ማብራሪያ፣ አምላክን ሦስት አድርገው ያቀርቡታል:: እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ፣ "ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል አንዱ" የሆነው ጀምስ ታልማግ፣ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሟች እንደ ሆኑት ሰብዓዊ ፍጡራን የተለያዩ አካላት

[3] ድርጅቱ "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?" በሚል ርእስ መለስተኛ መጽሐፍ አሳትሞ አሠራጭቷል:: የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ "አርዮሳውያን" እንዲሁም "ትምህርተ ሥላሴ መሠረታውያን" በሚል ርእስ ባዘጋጃቸው መጻሕፍት ይህን መጽሐፍ ተችቷል::
[4] "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን" (ኒውዮርክ፤ የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር 1989) ገጽ 8-12::
[5] በዚህ የሃይማኖት ተቋም ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ "ሰባልዮሳውያን" በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ሁለት ቅጽ መጽሐፍ ይመለከቷል::



ናቸው" ይላል[6]:: እንደ ድርጅቱ ትምህርት ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን፣ አምላክ የሚኖርበት (ያደረበት) ወይም በአምላክ ላይ የተለጠፈ ሥጋ (ቍሳዊ አካል) ነው::

ሜሪ ቤክር ኤዲ የምትባለው አሜሪካዊት ወይዘሮ የመሠረተችውና "ክርስቲያን ሳይንስ" በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ድርጅት፣ የክርስቶስን አምላክነት በመካድ የሥላሴን አስተምህሮ ይቃወማል:: ወይዘሮዋ፡— "ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ አይደለም፤ ነገር ግን እርሱ ራሱ እንዳስተማረው የእግዚአብሔር ልጅ ነው"[7] ትላለች:: ለእርሷ የእግዚአብሔር ልጅ ማለት አምላክ ማለት ሳይሆን፣ ከአምላክ ያነሰ ማለት ነው::

ዛሬ በዙሪያችን እንደ እንጉዳይ የፈሉት አባይ ነባዮች፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ "የእምነት እንቅስቃሴ" በሚባለው አግድም ዐደግ ትምህርት ክፉኛ የተበከሉ ናቸው:: በየስብከታቸው መኻል ሁሉ እያፈተለከ የሚወጣው ግልጠታቸውና ትንቢታቸው፣ ታሳቢ ያደረገው የእምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ ነው:: ብዙ አባይ ነባዮች፣ "ሰው አምላካዊ ባሕርዮት አለው" ወይም ከሰብአውያን ከፍ ያለ "ደርዝ"[8] አለን ባዮች ናቸው:: እንዲያውም አንዳንዶች በድፍረት እኛ አምላክ ነን እያሉን ነው[9]:: ይህ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት፣

[6] Gomes ገጽ 25 ከ*James Talmage, A Study of Articles of Faith (salt Lake City: The church of Jesus Christ of Latter-day Saints, 1976)*, አንቀጽ 1 ገጽ 29-51 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[7] Gomes ገጽ 26 ከ*Mary Baker Eddy. Science and Health with Key to the Scriptures (boston Trustees Under the Mary Baker G. Eddy, 1934)* ገጽ 361 ጠቅሶ እንደ ጻፈው::
[8] "*dimension*" ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል፣ እነርሱ ራሳቸው የሰጡት የአማርኛ ስያሜ ነው:: በዚህ ጉዳይ ኤልያስ አብጤ የተባለው አባይ ነባይ በቅርቡ በማኅበራዊ መገናኛ የሰጠውን መግለጫ ይመለከቷል::
[9] ነይሉ ዮሐንስ የተባለውም መናፍቅ፣ እኔ አምላክ ነኝ ሲል በኤልሻዳይ ቴሌቪዥን የተከራከረውን ቪዲዮ በናሙናነት ይመለከቷል::

"እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም" የሚለውን አስተምህሮ በቀጥታ የሚቃረን ነው። ሰይጣን "በልዑል እመስላለሁ" እንዳለው፣ አዳምና ሔዋንንም "እንደ እርሱ እንዳትሆኑ ፈልጎ ነው" ብሎ እንዳሳታቸው፣ ዛሬም ሳይጣን በግልጽ፣ "ሰው አምላክ ነው" የሚል ትምህርት ይዞብን ብቅ ብሏል። ይህ የአባይ ነባዮች ትምህርት ከትምህርተ ሥላሴ ጋር በጽኑ የሚቃረን ነው።

## 2. ድነት በእምነት አማካይነት በጸጋ መሆኑን መካድ

ቫን ባለን የተባለው ዐቅብተ እምነት፣ የሁሉም መናፍቃን የትምህርታቸው ማእከል፣ "ራስህን ማዳን አለብህ" የሚለው አስተምህሮ ነው ይላል። ይህ ደግሞ የመናፍቃኑ ብቻ ሳይሆን፣ የአባይ ነባዮቹም ትምህርት ነው። ለእግዚአብሔር ጸጋ የከንፈር አገልግሎት ብቻ እንዲሰጡ ያደረጋቸው፣ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ያከናወነውን (የፈጸመውን) የድነት ሥራ ስለሚያቃልሉ ነው። የክርስቶስ የድነት ሥራ በራሱ ሙሉ በሙሉ የማያድን ከሆነ፣ የጐደለውን በሥራ ማካካስ ወይም መሙላት የግድ ይሆናል።

አንዳንድ መናፍቃን የክርስቶስ የማዳን ሥራ፣ አንድ ሰው ወደ እምነት ከመምጣቱ በፊት ያለበትን ኀጢአት የማጠብ ኀይል አለው። ነገር ግን ወደ እምነት ከመጣ በኋላ ራሱን ማዳን ያለበት እርሱ ራሱ ወይም የእርሱ ድርጅት ወይም ደግሞ የድርጅቶቹ የአመራር አካላት በሚሠሩት ሥራ እንደ ሆነ አጠንክረው ያስተምራሉ። አንዳንዶች ደግሞ፣ የክርስቶስን የማዳን ሥራ ትናንሽ ኀጢአቶችን ብቻ እንጂ፣ ትላልቅ ኀጢአቶችን እንደማይጨምር ይገልጻሉ። የተቀሩት ደግሞ የክርስቶስ የድነት ሥራ ለሰው ልጆች ሁሉ እንደማይሆን፣ ነገር ግን እርሱ የጀመረውን ሥራ እነርሱ ከዳር እንደሚያደርሱ ይናገራሉ።



## አስረጅ

"ስይሖዋ ምስክሮች"፣ ድነት ለመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሙሉ በሙሉ ከመገዛትና በሚያወጣቸውም ፕሮግራሞች ተካፋይ ከመሆን ውጪ የሚታሰብ አይደለም[10]።

እንደ ሞርሞኖች ደግሞ አንድ ሰው ድነትን ማሰብ ያለበት፣ አምኖ ንስሐ ከገባ በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በድርጅቱ ሰዎች እጅ ተጭኖ ከተጸለየለት በኋላ ነው። እንደ "ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አስተምህሮ ኢየሱስ፣ አብ ነው ብሎ ማመን (በአብና በወልድ መካከል የማንነት ልዩነት የለም) እንዲሁም በትክክለኛው የጥምቀት ቀመር መጠመቅ ለድነት ወሳኝ ጉዳይ ነው[11]።

ዴቪድ ኮሬሽ የተባለው መናፍቅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ የማዳን ሥራው ሕያው የሚሆነው፣ እስከ 31 ዓ.ም ብቻ እንደ ሆነ ገልጾአል። ስለዚህ ከ31 ዓ.ም በኋላ ላለው የሰው ልጆች ኀጢአት እርሱ መሞት እንዳለበት ያስረዳ ነበር[12]።

ጥር 6 ቀን 1920 ዓ.ም በኮርያ የተወለደውና በኮርያ ተራራ ሥር፣ ከራሱ ከክርስቶስ ራእይ ተቀብያለሁ የሚለው ሳን ማዮንግ ሙን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የአካልና የመንፈስ ድነት ማምጣት ስላልቻለ ይህን ነገር ከዳር እንዲያደርስ እርሱ እንደ ተመረጠ፣ ይህንንም

---

[10] ለበለጠ ማብራሪያ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ፣ "እርዮሳውያን" በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

[11] ድርጅቱ አስተምህሮ ትክክለኛው የጥምቀት ቀመር፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ነው፤ ይህም ለድነት መሠረት ነው ይላል።

[12] *Gomes*፤ ገጽ 27 ከ*Talmage. A Study of the Articles of Faith.* እንቀጽ 4 ገጽ 107-108 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

ያበሰረው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ እንደ ሆነ ያገለጻል[13]። ኢየሱስ ክርስቶስ እውን ያደረገው ወይም በሞቱና በትንሣኤው የፈጸመው መንፈሳዊውን ድነት ብቻ ሲሆን፣ ሙን ደግሞ አካላዊውን ድነት ወይም ዐርነት እውን እንዲያደርግ የተመረጠ ሰው ነው።

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ውስጥ እኛ "ነቢያት ነን"፣ "ሐዋርያት ነን" የሚሉ ብዙዎች፣ "ከዘር ማንዘር የሚተላለፍ መርገም" እንዳለ እንዲሁም ይህ መርገም በእነርሱ "ቅባታዊ" አገልግሎት እንደሚሰበር ይገልጻሉ። እንዲያውም አንዳንዶች "ቅባታችን የመስበር ቅባት ነው" ሲሉ ተደምጠዋል። በርግጥ ክርስቶስ ኢየሱስ፣ በጐልጐታ ጣሩ በመስቀል ህማሙ ዕዳችንን ካልከፈለ፣ መርገማችንን ካልሰበረ የክርስቶስ ቤዛዊ ወጆ የተሟላ አልነበረም ማለት ነው። ስለዚህ የሚከተሉትን ተያያዥ ጥያቄዎች መጠየቅ አግባብ ከምንለውም በላይ ነው:— *(1)* ክርስቶስ ይህን መርገም ካልሰበረው፣ የትኛው ጉበዝ የእኛን መርገም ሊሰብር ይችላል? *(2)* ለእኛስ እነርሱ ይሰብሩልናል ብለን እናስብ፣ ነገር ግን የእነርሱን መርገም የሚሰብርላቸው ወይም የሰበረላቸው ማን ነው? *(3)* የአባቱንም ሆነ የቅድመ አያቶቹን የዘር ሐረግ በውል የማያውቅ ክርስቲያን፣ የመርገሙን ዐይነት በምን ዐውቆ ወደ ለበራው ምዕራፍ ሊሸጋገር ይችላል? *(4)* መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ፣ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኵነኔ የለባቸውም"፣ "ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን" (ገላ. 2÷13) እንዲሁም "ክርስቲያኖች ከዘላለም ሞት ወደሚደነቅ ብርሃን መጥተዋል"፣ "ዳግም በመወለድ የእግዚአብሔር ልጆች ሆነዋል"፣ "የአምላክ ቤተ

[13] ገዢ. ከማሁ፤ ከSamples eta., *Prophets of the Apocalypse* ገጽ 205 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።



ማደሪያ/መቅደስ ሆነዋል" ወዘተ በሚልበት ዐውድ (ሮሜ 8÷1፤1ዮሐ 3÷14፤ 1÷12፤ 3÷16)[14] እነዚህ ሰዎች፣ ከሥጋ ወላጆቻችሁ እየተንከባለለ የሚመጣ መርገም አለባችሁ እንዴት ሊሉን ይችላሉ?

## 3. የአካል ትንሣኤን መካድ

የክርስቶስ የአካል ትንሣኤ የክርስትና እምነት ያረፈበት ታሪካዊ መሠረት ነው (1ቆሮ. 15)። መናፍቃን ደግሞ መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ማጣመም ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። ትንሣኤን መንፈሳዊ የሚያደርገው ትምህርት በዚህ ረገድ ዋነኛው ነው። ይህ ትምህርት፣ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው ረቂቅ መንፈስ ሆኖ ነው የሚል ዐዋጅ አለው። ለዚህ ክሕደት ጥሩ አስረጅ የሚሆኑት "የይሖዋ ምስክሮች" ናቸው። እንደ መጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር፣ "ንጉሥ ክርስቶስ ኢየሱስ በሥጋ ሞቶ፣ የማይታይ ፍጥረት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል"[15] ይህ ብቻ አይደለም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት፣ የክርስቶስን ትንሣኤ አስመልክቶ እንዲህም የሚል ግምት አለው፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል፤ ወይም ለእግዚአብሔር ፍቅር ታላቅ መታሰቢያነት በአንድ ስፍራ ተጠብቆ ነው ያለው"[16]። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን እንደ ተነሣ ይናገራል[17]።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ፣ ክርስቶስ በ70 ዓ.ም መጥቷል የሚሉ ሰዎች

[14] ይህን ጉዳይ (በዚሁ ክፍል) ኋላ በስፋት እንተችበታለን።

[15] *Let God Be True* (1946)፤ ገጽ 22።

[16] *Studies in the Scripture*፤ ገጽ 129፤ ቅጽ 2።

[17] በሙታን ትንሣኤ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ፣ "በሥጋ ትንሣኤ አምናለሁ…" በሚል እርስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመልከቱ።

ተነሥተዋል፡፡ ክርስቶስ በ70 ዓ.ም ከመጣ ምጽአቱን ተከትሎ እውን ይሆናሉ ከሚባሉት ክሥተቶች መኻል አንዱ ትንሣኤ ሙታን ነው፡፡ እነዚህ ግለሰዐች የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በ70 ዓ.ም እውን ሆኗል ብቻ ሳይሆን፣ ትንሣኤ ሙታንም ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ነው እያሉ ነው፡፡ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በተመለከተ የነገረ መለኮት ምሁራን የተለያየ አስተያየት እንዳላቸው እሙን ነው፡፡ ነገር ግን ምጽአቱ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ተጠናቋል የሚለውን ትምህርት ለማጽናት፣ ዐበይት የሚባለውን የትንሣኤ ሙታንን አስተምህሮ መካድ ትልቅ ስሕተት ነው፤ ኑፋቄ ነው፡፡

በርካታ አባይ ነባዮች ቊስ አካል እርኩስ መንፈስ ደግሞ ቅዱስ ነው የሚለውን የጥንት ኖስቲኮችን ኑፋቄ ይዘው መጥተዋል፡፡ ሥጋ ትንሣኤን የሚጠብቅ በክርስቶስ የተዋጀ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ/ማደሪያ ሳይሆን፣ ነፍስና መንፈስ የታሰሩበት ከርቸሌ/እስር ቤት ነው፡፡ "ሰው መንፈስ ነው፤ ነፍስ አለው፤ በሥጋ ውስጥ ይኖራል" ባዮች ናቸው፡፡ አባይ ነባዮቹ፣ "አንተ በሥጋ ውስጥ የምትኖር እንጂ ሥጋ አይደለህም" የሚለው ትምህርታቸው ለሥጋ ትክክለኛ ዐታ ያለመስጠታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሥጋ ማደሪያዬ እንጂ ማንነቴ ካልሆነ፣ "በሥጋ የምሠራው ማናቸውም ኀጢአት እኔን ሊነካኝ ወይም በተጠያቂነት ውስጥ ሊጥለኝ አይችልም" ከሚለው የኖስቲኮች አሮጌ ኑፋቄ ጋር አንድ ዐይነት ነው፡፡

## 4. መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም ሥልጣናዊ ቃል መሆኑን መካድ

አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ መጽሐፍ ቅዱስ በስሕተት እንደ ተሞላ ይናገራሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ሥልጣናዊ ቃልነቱን በመቀነስ፣ "አሮጌው ብርሃን" በማለት ይጠሩታል፡፡ ይህም፣ "አዲሱ ብርሃን" ከሚሉት ከእነርሱ አስተምህሮ ማነሱን ለማሳየት ነው፡፡



ሌሎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደ ሆነ ቢናገሩም፣ መጽሐፍ ቅዱስን "የሚተረጕሙት" ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር እንዲስማማ አድርገው ነው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣናዊነት የሚያቃልሉት፣ ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም አድርገው በማብራራት ነው፤ እነዚህ የማብራሪያ ጽሑፎች ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ይታያሉ፡፡

## አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል እንደ ሆነ፣ የአስተምህሮና የሥነ ምግባር መሠረት እንደ ሆነ ይገልጻሉ፤ ነገር ግን ከድርጅቱ አስተምህሮ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ የተዘጋጀው መጽሐፍ (የአዲሱ ዓለም ትርጉም) ድርጅቱ በተደጋጋሚነት የሚያውጀውን ዐዋጅ ከልብ እንዳልተቀበለው የሚገልጽ ነው፡፡ የአዲሱ ዓለም ትርጉም ያለምንም ቃለ እግዚአብሔርና የታሪክ ማስረጃ ያህዌ (ጆሆቫ) የሚለውን ስም በአዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ 237 ጊዜ በላይ መጠቀሙ፣ ድርጅቱ ኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነትና የሥላሴን አስተምህሮ ለመቃወም ምን ያህል እንደ ጠቀመው፣ ቃሉን በተጠቀሙባቸው ዐታዎች ሁሉ በግልጽ መረዳት ይቻላል፡፡

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ዮሴፍ ስሚዝ፣ የእርሱን መምጣት የሚያበሥር "ትንቢት" ይሆን ዘንድ፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 50 ላይ 14 ቊጥሮችን ጨምሮበታል፡፡ የሞርሞን የእምነት አንቀጽ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ከተተረጐመ፣ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ እንዲሁም የሞርሞኖች መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ እናምናለን"[18] ይላል፡፡ ይህ ብቻ

[18] *Gomes* ገጽ 30 ከ*Articles of Faith Article 8* ጠቅሶ እንደ ጻፈው፡፡

አይደለም ዋልተር ማርቲን፣ ሞርሞኖች መጽሐፍ ቅዱስን ከራሳቸው መጽሐፍ ጋር እንኳ እኩል እንደማያዩት ያስረዳል። ሞርሞኖች ቃለ እግዚአብሔርን የሚያዋርዱት ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል የሚታይ መጽሐፍ በመጨመር፣ ከእነርሱ መጽሐፍ ጋር በማይታረቅበት ቦታ ሁሉ እንዲጣጣም ተደርጎ እንዲተረጐም ከማድረግ ባሻገር፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጨማሪ ምዕራፍና ቊጥር በመጨመርም ነው።

በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ያሉት ነባዮች፣ "አዲስ መገለጥ እንንገራችሁ ወይስ ስጥቊሩ መጽሐፍ አሮጌ መገለጥ እናንብብላችሁ" ማለት ጀምረዋል። ይህ ቅዱሳት መጻሕፍት ዛሬም ሲናገሩን፣ ሲመክሩን፣ ሲገሥጹን ወዘተ ሕያው/ትኩስ ናቸው የሚለውን መሠረታዊ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መሠረተ እምነት በቀጥታ የሚጻረር ትምህርት ነው። አንዳንዶች ደግሞ አስተምህሮዎችም ሆኑ ግለሰቦች መመዘን ያለባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይሆን፣ በእነርሱ መንፈሳዊ "ከፍታ" አንጻር እንደ ሆነ በማግለጽ ላይ ናቸው። "እኔ ስባተኛ ክልል ነኝ ስለዚህ እናንተ ለመመዘን ብቃት የላችሁም፤ ያን ዐይነት ምዘና ማካሄድ የሚኖርብን፣ ከፍ ብለን የምንገኘው እኛ ነን"[19] አያሉ ነው። ይህ አካሄድ የአንድን ትምህርትና የአንድን ግለሰብ አካሄድ የሚመዝነው፣ ቀኖናዊ መጻሕፍት የሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ሳይሆኑ፣ ግለሰቦች ናቸው ማለት ነው። ይህ የአስተምህሮና የሥነ ምግባር መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ከሚለው መሠረታዊ የክርስትና አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነው።

[19] አባይ ነባይ ኤልያስ አብሬቤ በቅርቡ ያሠራጨውን ቪዲዮ ይመለከቷል።



## 5. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ መተርጐም

አብዛኛውን ጊዜ መናፍቃን ለክርስቲያናዊ ቃላት አዲስ ትርጓሜ መስጠት ይወዳሉ። ስዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ በ2ቆሮ 11÷4 ላይ፣ ሐዋርያት ከሰበኩት የተለየ (ገላ 1÷6-9) "ሌላ ክርስቶስ"፣ "ሌላ መንፈስ"፣ "ሌላ ወንጌል" የሚለውን አጠቃቀም ሲጠቀም የሚስተዋለው። አባይ ነባዮችና መናፍቃን ስለ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል፣ ስለ ድነት ወዘተ አብዝተው ይናገራሉ፤ ነገር ግን እነዚህን ቃላት የሚጠቀሙት መጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን በሚተረጕምበት መንገድ አይደለም። ዋልተር ማርቲን እንደሚለው፣ "ብዙውን ጊዜ ከመናፍቃን ጋር የምናደርገው ውይይት ፍሬ አልባ የሚሆነው፣ ለምንወያይባቸው ጉዳዮች ትክክለኛውን ትርጉም (ገለጻ) ባለመጠየቃችን ነው"[20]። ክርስቲያኖች ከመናፍቃን ጋር የሚያደርጉት ውይይት ስኬታማ ሊሆን የሚችለው፣ መናፍቃኑ ቊልፍ የሆኑ ቃላትን እንዴት እንደሚመለከቷቸው አስቀድመው የሚያውቁ ከሆነ፣ አለያም በውይይቱ ወቅት እንዲብራራላቸው በመጠየቅ ብቻ ነው።

## አስረጅ

"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አማኞች በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን ይላሉ። አንደ ድርጅቱ አስተምህሮ አብ እግዚአብሔር፣ ወልድ ሰው ብቻ፣ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ የአብ ሌላው ስም ነው። ስለዚህ አንድ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አባል በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ ቢለን፣ ግለሰቡን በሥላሴ አማኚ ነው ማለት እንዳልሆነ ልብ ልናደርግ ይገባል።

[20] *Martin, Kingdom of the Cults* ገጽ 10።

"ይሖዋ ምስክሮች" ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን እናምናለን ይላሉ፤ ይህን ማለታቸው ግን "ሰይጣን የዚህ ዓለም አምላክ"፣ "ሙሴ የፈርዖን አምላክ" በተባለበት ሒሳብ እንጂ፣ "እንደ አብ ሁሉን ቻይ አምላክ ማለት አይደለም" ይላሉ። ስለዚህ "የይሖዋ ምስክሮች" ኢየሱስን አምላክ ቢሉ፣ አምላክ ነው ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው የሚል ማብራሪያ እንዲሰጠን መጠየቅ አለብን።

የእምነት እንቅስቃሴን አስተምህሮ የተቀበለ ሰው፣ "ዳግም ተወልደሃል" ብሎ ቢጠይቅ፣ የእግዚአብሔር ልጅ ሆነሃል ማለቱ ሳይሆን፣ "የእግዚአብሔርን ባሕርይ ገንዘብ በማድረግ፣ እግዚአብሔር ሆነሃል" ማለቱ ነው[21]።

## 6. አባይ ነባዮችና መናፍቃን ድርጅቶቻቸውና መሪዎቻቸው የእግዚአብሔር ብቸኛ እንደራሴዎች እንደ ሆኑ ይናገራሉ

አባይ ነባዮችም ሆኑ የመናፍቃዊ ድርጅት መሪዎች፣ የእግዚአብሔር ብቸኛ ወኪሎች፣ ድርጅታቸውም በአምላክ የሚመራ ብቸኛ ድርጅት፣ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚገናኝባቸው ድልድዮች፣ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ መገለጥ ተቀባዮች አድርገው ራሳቸውን ያቀርባሉ።

ነገር ግን ይህን የመናፍቃን ዐዋጅ ክርስቶስ፣ "እኔ መንገድና ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" ከሚለው ወይም የክርስቶስ ሐዋርያት፣ "መዳንም በሌላ በማንም የለም አንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ

[21] ለበለጠ ማብራሪያ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ ከወንድም ምኒልክ አስፋው ጋር፣ "የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ?" በሚል ርእስ ያዘጋጁትን መጽሐፍ ይመለከቷል።



የለምና" (ሐሥ 4፥12) በማለት ኢየሱስ ክርስቶስን የእግዚአብሔር ብቸኛ እንደ ራሴ (ወኪል) ከማድረጋቸው ጋር በማነጻጸር፤ ዐዋጁን ወግድ ከማለትም ባሻገር፣ አስተምህሮውን በግልጽ ልንቃወመው ይገባል። ይህ የአምላክን የድነት መንገድ የሚጻረፍ፣ እኩይ ትምህርት ናውና።

## አስረጅ

"የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት፣ የአምላክ ፍጹም ብቸኛ ድርጅት እንደ ሆነ ይገልጻል። የድርጅቱ ሥልጣናዊ መዋቅር "ታማኝና ልባም በሆኑ ባሮች" እንደ ተሞላ፣ እነዚህም "ባሮች" ወቅታዊ የሆነውን መንፈሳዊ ምግብ ከአምላክ በወቅቱ እንደሚያወርዱ፣ የእግዚአብሔር እንደ ራሴዎች ይታያሉ[22]። ሁሉም "የይሖዋ ምስክር" ያለምንም ጥያቄና ቅድመ ሁኔታ ትምህርታቸውን መቀበልና መታዘዝ ይጠበቅበታል።

"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ ድርጅት፣ ሰዎች የዘላለምን ሕይወት የሚያገኙት፣ በእነርሱ ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ሲጠለሉ ብቻ እንደ ሆነ ያስተምራል። ትክክለኛ ትምህርት ባላት አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አባል መሆን፣ የታላቁን ተልእኮ ሥራ ለማከናወን እንዲሁም በክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወት ለማደግ ጠቃሚ ጉዳይ መሆኑ ቅቡል ነው። ይህ ማለት ግን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያልታቀፈ ሰው ድነት አያገኝም ማለት አይደለም። በየትኛውም የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር መጠለል፣ ድነት የማግኛ ቅድመ ሁኔታ አይደለም፤ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ መቀበል እንጂ።

[22] *You can Live Forever in Paradise on Earth* (1982) ገጽ 191-195።

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ውስጥ የምናገኛቸው በርካታ ነባዮች፣ የእነርሱን ፕሮግራም መካፈል እንዲሁም የእነርሱን የቴሌቪዥን ፕሮግራም መከታተል፣ ለመንፈሳዊ ዕድገት ዋነኛ ጉዳይ ከመሆኑም ባሻገር፣ ሰዎች "መንፈሳዊ ቅባት የሚቀቡት"፣ "ከዘር ማንዘር መርገም የሚያመልጡት" የእነርሱን ፕሮግራም በአንክሮ በመከታተል እንደ ሆነ ይገልጻሉ። በእንጻሩ ፕሮግራሞቻቸውን ያለመካፈል፣ ከትልቅ የአምላክ በረከት መጉደል ነው።

እንዲያውም በቅርቡ፣ አባይ ነባዮቹ በበርካታ የአሜሪካን ክፍለ እገሮች ቤተ ክርስቲያን በመትከል ሰዎች የአገልግሎታቸው ተጠቃሚ እንደሚሆኑ መግለጻቸው፣ ከዚህ አሳብ ጋር የሚጉዳኝ ነው። በርካታ ተከታዮቻቸውም እነዚህን ግለሰቦች፣ "አባት" በማለት መጥራታቸው ሳያንስ፣ ያለእነዚህ ግለሰቦች ክርስትና ሕይወት የማይሞከር ጉዞ እንደ ሆኑ በመግለጽ ላይ ናቸው።

## 7. ከአስተምህሮአቸው ጋር የሚቃረኑ እውነቶችን፣ ከቍብ አይቈጥሯቸውም

በርካታ መናፍቃን ከቦዋኛቸው ጋር የሚቃረኑ እውነቶችን ትኩረት አይሰጡአቸውም፤ ወይም አናንቀውና አድበስብሰው ያልፏቸዋል።

### አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" ሲፈጸሙ (እውነት ሲሆኑ) ያልታዩ በርካታ የሐሰት ትንቢቶችን ተንብየዋል፤ ነገር ግን ይህንን አስተምህሮ እንዲያዋቅሩ ያደረጓቸውን የነቢያት መጻሕፍትን የሚተረጉሙበትን ዘዴ እሁንም አልቀየሩም። የአርማጌዶን ጦርነት በ1914 ዓ.ም ይሆናል ተብሎ ነበር፤ በዚህ ወቅት ሲሆን ሳይችል በመቅረቱ ቀኑ ወደ 1915 ዓ.ም ከዚያም 1975 እና 1981 ዓ.ም



ተሸጋገረ[23]። ነገር ግን ይህን መሰሉን ትንቢት የተናገረው ድርጅት አሁንም ራሱን ከአምላክ እውነተኛ ትንቢት ተቀባይ አድርጎ ይቈጥራል።

ሞርሞኖች "የሞርሞን መጽሐፍ" የተባለውን መጽሐፋቸውን 3,913 ጊዜ ስሕተቱን አርመዋል[24]። ነገር ግን አሁንም ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል፣ "በምድር ላይ ፍጹም ስሕተት የሌለበት መጽሐፍ"[25] ይባላል።

ክርስቲያን ሳይንስ የተባለውን መናፍቃዊ ድርጅት የመሠረተችው ሜሪ ቤከር ኤዲ፣ በሽታ እውነትነት የሌለው ሕልም (ቅዠት) ነው ብትልም፣ እርሷ ራሷ ታማ በዶክተር ትረዳ እንደ ነበር፣ የሕመም ማስታገሻ መርፌ እንደምትወጋ፣ አጥርታ እንድታይ የሚረዳት መነጽር ታደርግ እንደ ነበር፣ በሕመም ምክንያት ብዙ ጥርሶቿን እንዳጣች ይታወቃል[26]። ነገር ግን ዛሬም የኤዲ ተከታዮች በሽታ እውነትነት የሌለው ቅዠት ነው የሚል አቋም አላቸው[27]።

በውስጣችን ያሉ በርካታ አባይ ነባዮች፣ ተከታዮቻቸው ቱጃር እንደሚሆኑ፣ እንዳችም በሽታ እንደማያገኛቸው፣ እርግማናቸው ስለተሰበረ በተትረፈረፈ ሀብት ውስጥ እንደሚዋኙ ይገልጻሉ። ነገር ግን ተከታዮቻቸው ጊዜያዊ የስሜት ብፍታ ካልሆነ በስተቀር እውነተኛ የሆነ ለውጥ በዚህ ረገድ እንዳላገኙ እየታየ ነው። ቱጃር ሊሆኑ የታዩት አባይ ነባዮቹ እንጂ፣ የአባይ ነባዮቹ አገልግሎት ተጠቃሚ አይደሉም። ነገር ግን ትላንት የተታለለው

---

[23] *የመጠበቂያ ግንብ (ሚያዝያ 1 ቀን 1972)*። በወቅቱ የነበሩ ብዙ "የይሖዋ ምስክሮች"፣ በዚህ ምክንያት ድርጅቱን ለቀው ወጥተዋል።

[24] *Martin, Kingdom of the Cults* ገጽ 29።

[25] በ1991 ዓ.ም የታተመው "የሞርሞኖች መጽሐፍ" መግቢያ ላይ፣ ጆሴፍ ስሚዝ ያስፈረው ዐረፍተ ነገር ነው።

[26] *Martin, Kingdom of Cults* ገጽ 29።

[27] ዝኒ ከማሁ።

ሰው፣ ምናልባት ዛሬ እውነት ሊሆን ይችላል በሚል ይከተላቸዋል። እነርሱም "አንተ እምነት ስለሌለህ ነው" ወይም "ወፈር ያለ ዐሥራት ስላልሰጠህ ነው" ወይም "ፊውስህ ቀስ በቀስ ይበቅላል ስለዚህ ታገሥ" በሚሉ ወጊሻዎች እየታሹ፣ አብረዋቸው በመዝለቅ ላይ ናቸው። እንዲያውም አንዳንድ አባይ ነባዮች በውል የሚታይ የዐይንና የአካል ችግር እያለባቸው እኛ ዘንድ የመጣ ይፈወሳል እያሉ በድፍረት ያውጃሉ።

## 8. የዘላለም ኩነኔን (ቅጣት) መካድ

በርካታ አባይ ነባዮችም ሆኑ መናፍቃን፣ የእግዚአብሔር ቃል ስለ ዘላለም ቅጣት የሚያስተምረውን እውነታ አይቀበሉም። አንዳንዶች ለምሳሌ የመላለማዊ *(universalism)* ትምህርት አራማጆች፣ የሰው ልጆች ሁሉ የዘላለምን ሕይወት እንደሚያገኙ ሲያስተምሩ ለሌሎች ደግሞ፣ አምላክ ኀጢአተኞችን ወደ አለመኖር ደረጃ ይወስዳቸዋል ("ብን ብለው እንዲጠፉ *annihilate* ያደርጋቸዋል" ይላሉ)።

## አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" በድርጅት መልክ ተዋቅረው መንቀሳቀስ ከጀመሩ 120 ዓመት ይሆናቸዋል። በእነዚህ ዘመናት ሁሉ ኀጢአተኞች ዘላለማዊ ቅጣት ይጠብቃቸዋል የሚለውን ትምህርት አጥብቀው ሲቃወሙ ኖረዋል። የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዝዳንት የነበረው ጆሴፍ ፍራንክሊን ራዘርፎርድ፣ "የዚህ [የዘላለም ቅጣት] እግዚአብሔርን የማያከብር አስተምህሮ ጠንሳሽ ሰይጣን ነው። ይህንን ያደረገበትም ምክንያት፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል



እንዳያነቡ ለማስፈራራት እግዚአብሔርን እንዲጠሉ ለማድረግ ነው"[28] ብሎአል።

ዩኒቴሪያን ዩኒቨርሳሊስት የተባሉት መናፍቃን፣ የሥላሴን አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን፣ የዘላለም ኩነኔንም ይቃወማሉ። እንዲያውም የድርጅቱ መሠረተ እምነት ሰው ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዳለው ይገልጻል[29]።

በርካታ አባይ ነባዮች በኀጢአት ውጤት ወይም የተፈጥሮ ሕግጋት በሆኑት በመንሥኤና በተገብሮ እንኳ የሚያምኑ አይደሉም። ማጣትንና ህማምን ሁል ጊዜ የሚያብራሩት ከመርገም ጋር እያያዘው ብቻ ነው። ስንፍና፣ አባካኝነት፣ ያለማወቅ/ያለመማር፣ መልካም አስተዳደር ያለመኖር፣ የሰላም ዕጦት ወዘተ የድኽነት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

## 9. ከአስተምህሮአቸው ይልቅ ስልምምዳቸው ትኩረት መስጠት

መናፍቃንም ሆኑ አባይ ነባዮች፣ ከእውነትና ከምክንያታዊ አስተሳሰብ ይልቅ፣ ለስሜት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ። በዚህ መሰሉ እንቅስቃሴ ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ አስተምህሮአችን ከእግዚአብሔር ቃል የመነጨ ነው ወይ? ለሚለው ጥያቄ ሳይሆን፣ ጥሩ ስሜት ተሰምቶኛል ወይ? ከቀድሞ ልምምዴ ጋርስ ይስማማል ወይ? ለሚለው ትልቅ ትኩረት ይሰጣሉ። ስሜትና የግል ልምምድ መጥፎ ነው ለማለት አይደለም። ነገር ግን ስሜትም ሆነ ልምምድ ተገቢ

---

[28] *Rutherford, Let God Be True* ገጽ 79፤ በቅንፍ ያለውን አይጨምርም። ይህን ትምህርት አስመልክቶ ያለውን የድርጅቱን ትምህርት ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር ገጽ 98-100፤ 168-175፤ 375-379፤ 382-383 እንዲሁም *You Can Live Forever in Paradise on Earth* ገጽ 76-89 ይመልከቱ። ይህን ርእስ ጉዳይ ጸሓፊው "አርዮሳውያን" በተሰኘው መጽሐፉ በሰፋት መርምሮታል።

[29] *Mather and Nichols, Dictionary* ገጽ 286።

የሆነውን ስፍራ መያዝ አለባቸው። ይኸውም ስቃስ እግዚአብሔር ትምህርት እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ለሚጣጣሙ ሳይንሳዊና ምክንዮአዊ ማስረጃዎች መገዛት አለባቸው:—

"እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ *(mind)* ውደድ" ይላል (ዘዳ. 6፥5፤ ማቴ. 22፥37፤ ማር. 12፥30፤ ሉቃ. 10፥27)። ይህ ዐይነቱም አምልኮ እውነትን ከስሜት ጋር አጣምሮ የያዘ ነው። የክርስትና፣ እውነት የተመሠረተው በማይነቀሉ በማይገሠሡ እውነታዎች ላይ እንጂ፣ በስሜት ላይ እንዳልሆነ ሲጠፋን አይገባም።

## አስረጅ

የእባይ ነባዮችን አስተሳሰብ አስተምህሮ በስፋት የቀረጸው፣ "የእምነት እንቅስቃሴ ትምህርት" ዕውቀትን "የስሜት ዕውቀት" እና "የመገለጥ ዕውቀት" ብሎ በመከፈል፣ ሃይማኖታዊ እውነታዎች በአምስቱ የስሜት ሕዋሳቶቻችን የምንገበያቸው ሳይሆኑ፣ በመገለጥ ብቻ የምናውቃቸው እንደ ሆኑ ያስተምራል። እንዲያውም ወደ "መገለጥ ዕውቀት" ለመግባት በስሜት ሕዋሳቶቻችን የሚታወቁትን እውነታዎች "መካድ" እንደሚያስፈልግ አጠንክሮ ያስረዳል። እንደዚህ እንቅስቃሴ ትምህርት ከሆነ፣ የስሜት ሕዋሳቶቻችንንም ሆነ እእምሮአችንን መጠቀም ሥጋዊነት ነው፤ የእግዚአብሔር እውነት በአእምሮ እንዲሁም በስሜት ሕዋሳት ፈጽሞ አይታወቅም ባይ ነው። ከዚህ የተነሣም ክርስቲያናዊ እውነቶችን በቃስ እግዚአብሔር መመርመር አይፈቀድም[30]። በእንቅስቃሴው ተከታዮች ዘንድ እንደ ትልቅ የእግዚአብሔር ሰው የሚቈጠሩት ኬኔት ሐጊን፣ አትተች፤ ግን "እግዚአብሔር እንዲገልጥልህ ጸልይ"[31] የሚለው አነጋገራቸው

[30] *Kenneth Hagin, I Believe in Visions (Old Tappan N. J.: Fleming H. Revell, 1972).*
[31] *Kenneth Hagin, The Voice of Healing (Apr. 1963).*



በጽሑፋቸው ተደጋግሞ የሚዘወተረው፣ መንፈሳዊ እውነትን በእእምሮአችን መረዳት አንችልም ስለሚሉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በስሜት ሕዋሳቶቻችን የምናውቃቸው ዕውቀቶች፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው መገለጥ ጋር ይቃረናሉ የሚል ትምህርት የለውም። እንዲያ ከሆነ በስሜት ሕዋሳቶቻችን የምናውቃቸው ዕውቀቶች ሁሉ ቅዠት ናቸው ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን አንብበን የምንረዳውም በስሜት ሕዋሳቶቻችን እንጂ፣ በመንፈስ አይደለም[32]።

ሞርሞኖች፣ "መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን" (ሉቃ 24፥32) የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ፣ እውነት እውነት መሆኑ የሚረጋገጠው፣ "ልባችን የሚቃጠልብን" ከሆነ ብቻ ነው ይላሉ። ለሞርሞኖች የእውነት መመዘኛው ሚዛን "የልብ መቃጠል" እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ደግሞ አመክንዮ አይደለም።

ብዙ ክርስቲያኖች የትምህርተ ወንጌልንም ሆነ የስብከተ ወንጌልን ትክክለኝነት የሚያጸድቁት፣ በወቅቱ በሚሰማቸው ስሜት ነው። በተስይ እሳት ልሶ እሳት ጐርሶ የሚያወራ ሰው ሁሉ በመንፈስ እንደ ተነዳ ይታሰባል።

## 10. ከእግዚአብሔር በቀጥታ ተቀብለናቸዋል ለሚሏቸው መገለጦችና ራእዮች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት

እባይ ነባዮች እንዲሁም መናፍቃን በተለይም የእንቅስቃሴው መሪዎች፣ ከእግዚአብሔር ጋር እስን ከሚሉት ቀጥተኛ ግንኙነት የተነሣ፣ ራእይና መገለጥ እንደሚወርድላቸው እንዲሁም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሆነውን መንፈሳዊ ምግብ የሚሰጠው

[32] በዚህ ረገድ ኀይሉ ዮሐንስ እንዲሁም የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን የሚያስተምሩትን ትምህርት፣ ከድረ ገጾች ላይ፣ በስፋት መመልከት ይቻላል።

በእነርሱ በኩል ብቻ እንደ ሆነ ይገልጻሉ። አብዛኛውን ጊዜ መገለጦቻቸውና ራእዮቻቸው ትኩረት የሚያደርጉት የመጨረሻውን ዘመን በተመለከተ ሲሆን፣ የእነርሱ ዕጣ ፈንታም ምን እንደ ሆነ፣ ከራእዩና ከትንቢቱ ጋር ተያይዞ ይቀርባል። ይኸውም እነርሱ ዋና ተዋናይ እንደ ሆኑ፣ ተከታዮቻቸውም በሂደቱ ውስጥ ቊልፍ ሚና እንዳላቸው የሚያስረዳ ነው። ቃለ እግዚአብሔር፣ "ሁሉንም መርምሩ፤ መልካሙን ያዙ" (1ተሰ 5÷21) ይለናል፤ የተነገረው ትንቢት እንደ ተባለው ካልተፈጸመ፣ ትንቢቱም ሆነ ነቢዩ ከእግዚአብሔር አይደሉም (ዘዳ 18÷22)። የአንድ ትንቢት ወይም መገለጥ ትክክለኛነት የሚረጋገጠው ትንቢቱ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በመስማማቱ እንዲሁም ተፈጻሚነት በማግኘቱና ባለማግኘቱም ጭምር ነው (ኢሳ. 8÷20)።

## አስረጅ

የሞርሞንን እምነት የመሠረተው ጆሴፍ ስሚዝ፣ በ1820 ዓ.ም ላይ እግዚአብሔር አብን እንዲሁም ወልድን በራእይ እንደ ተመለከተ ይገልጻል። ስሚዝ በዚህ ራእይ፣ ከየትኛውም ሃይማኖታዊ ድርጅት ጋር እንዳትገጥም ተብያለሁ ባይ ነው። ምክንያቱም:— "ሁሉም የሃይማኖት ድርጅቶች የተሳሳቱ ስለሆኑ" እንዲሁም "የሃይማኖት መግለጫቸው ሁሉ ጸያፍ ነው"[33] ባይ ነው። በመስከረም 21 ቀን 1823 ዓ.ም ሞሮናይ የተባለው መልአክ እንደ ተገለጠለትና፣ የሞርሞን መጽሐፍ ምን መሆን እንዳለበት የሚገልጹ የወርቅ ሳሕኖች እንደ ሰጠው ተናገረ። ሞሮናይ የተባለው መልአክ በ1827 ዓ.ም ዳግም ይገለጥለትና ሳሕኖቹን ቈፍሮ በማውጣት የትርጉም ሥራ እንዲጀምር ፈቃድ ይሰጠዋል። በወርኀ ግንቦት 1829

[33] *Gomes* ገጽ 37 ከ*Pearl of Great Price (1851, rev. ed, salt Lake City: Church of Jesus Christ of Latter-day saints, 1981)*: 19 ላይ ጠቅሶ እንደ ጻፈው።



ዓ.ም መጥምቁ ዮሐንስ፣ ለስሚዝና ለኦሊቨር ኮድሪ ይገለጥላቸውና አሮናዊ ክህነት እንደ ተሰጣቸው ያረጋግጥላቸዋል[34]። ጆሴፍ ስሚዝ ከሞተ በኋላ፣ ድርጅቱን የመምራት ኀላፊነት የተረከበውና "የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት" መሪ የሆነው ብሪጋሃም ያንግ፣ "እኔ ስለራሴ ያየሁትና የሰማሁት በርካታ መገለጥ አለኝ፤ እነዚህም ነገሮች እውነት እንደ ሆኑ ዐውቃለሁ፤ በምድር ላይ የሚኖር አንድም ሰው እነዚህን ነገሮች ትክክል አይደሉም ማለት አይችልም"[35] ሲል ይገልጻል።

ይህ ብቻ አይደለም የሞርሞን ሐዋርያት፣ አውን ሲሆኑ ያልታዩ በርካታ ትንቢቶችን ተናግረዋል። በአሜሪካን አገር ተከሥቶ ስለነበረው የእርስ በርስ ጦርነት፣ ጆሴፍ ስሚዝ ታላቋ ብሪታንያ ከሰሜኑ ክፍል ጋር ተሰልፋ የደቡቡን ክፍል እንደምትወጋ የሚገልጽ ትንቢት ተናግሮ ነበር፤ ከጦርነቱ በኋላ ግን ትንቢቱ ፍጹም ሐሰት መሆኑ ተረጋግጦአል[36]።

"የይሖዋ ምስክሮች" ከ1935 ዓ.ም ጀምሮ የስብከት አቀጣጫቸውን በመቀየር፤ "ምድር ገነት ትሆናለች" እንዲሁም "ሰማያዊውን አካል የሚወርሱት የቅቡዓን (የ144 ሺህ) ቊጥር ሞልቶአል" ማለት ጀምረዋል። ይህን ማለት የጀመሩት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ስላላቸው ሳይሆን፣ የድርጅቱ ፕሬዚዳንት የነበረው ጆሴፍ ፍራንክሊን ራዘርፎርድ፣ በ1935 ዓ.ም "የቅቡዓን ቊጥር

[34] መጽሐፍ: ቅዱስ አሮናዊ ክህነት የተሰጣቸው ለሌዊ ልጆች ብቻ እንደሆነ ይነግረናል (ዘፀ. 4÷14፤ 29÷1)። እግዚአብሔር አምላክ ይህን የክህነት አገልግሎት ለሌዊ ልጆች የሰጣቸው፣ የእስራኤል ልጆችን ወክለው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ነው (ዕብ. 5÷1-3)። ከኢየሱስ ሞት በኋላ ሌዋዊም ሆነ አሮናዊ ክህነት አያስፈልግም።

[35] *Gomes* ገጽ 38።

[36] *Mc Dowell and Stewart, The Deceivers,* ገጽ 104-122።

ሞልቶአል፣ ከአሁን በኋላ "የይሑዋ ምስክር" የሚሆኑ ሰዎች የሚወርሱት ምድርን ነው" በማለት ስለተናገረ ብቻ ነው[37]።

የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የነበረው ሰን ምዩንግ ሙን፣ በ1936 ዓ.ም ኢየሱስ እንደ ተገለጠለትና ኢየሱስ የጀመረውን ሥራ እርሱ ከዳር እንደሚያደርስ እንደ ተነገረው ይገልጻል[38]።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትን በማመስ ላይ የሚገኙት ዘመነኞቹ አባይ ነባዮች፣ ትንቢታችሁ ለምን አልተፈጸመም የሚለውን ጥያቄ የሚያዳፍኑት፣ "እኛ ከደረስንበት መንፈሳዊ ዓለም አልደረሳችሁም"፣ "ብንነግራችሁም አይገባችሁም" እያሉ ነው። አንዳንዶች ደግሞ፣ "የነቢይን ትንቢት መመርመር የሚችለው ነቢይ ብቻ ነው" እንዲያውም "በእኩል መንፈሳዊ ደርዝ/ደረጃ የሌለ ነቢይ"፣ ከእርሱ በላይ የሆነውን ትንቢት እንኳ መመርመር አይችልም ይላሉ[39]። ይህ ነገሩን ፍጹም ምስጢራዊ በማድረግ፣ ራሳቸውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ምርመራ ለመደበቅ የሚያደርጉት ጥረት እንደ ሆነ፣ አማኙ ማኅበረሰብ በግልጽ ሊረዳ ይገባዋል። መጽሐፍ ቅዱስንም መሠረት በማድረግ ግብራቸውንም ሆነ ትንቢታቸውን በጥልቀት መመርመር ይጠበቅበታል።

## 11. ለድንቆች፣ ለምልክቶችና ለተኣምራት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ

ሁሉን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር፣ በእውነተኛ ክርስቲያኖች አማካይነት ድንቅና ተኣምራትን ሊያደርግ ይችላል። ነገር ግን መሠረታዊውን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ የሚክዱ ሰዎች በእግዚአብሔር ኀይል ተኣምራትን ሊያደርጉ በፍጹም

[37] ተስፋዬ ሮበሌ፤ *አርዮሳውያን*።

[38] *Gomes* ገጽ *38*።

[39] የኤልያስ አብጤን ቪዲዮ ይመለከቷል።



አይችሉም (ዘዳ. *18፥22*፤ ኢሳ. *8፥22*)። ነገር ግን ተኣምራትን ካደረጉ ተኣምራቱ ከእግዚአብሔር ሳይሆን፣ እንደ ሐዋርያው ቃል፣ "በሐሰተኞች ድንቆችም በዐመፅም መታለል ሁሉ እንደ ሰይጣን አሠራር ነው" *(2ተሰ. 2፥9-10)*።

## አስረጅ

ክርስቲያን ሳይንስ የተባለው መናፍቃዊ ድርጅት፦ ፈውስ ሊካሄድ የሚችለው፣ "በክርስቲያን ሳይንሶች ቀመር ብቻ ነው" የሚል አስተምህሮ አለው። ድርጅቱ፣ "ኤ ሴንቸሪ ኦፍ ክርስቲያን ሳይንስ ሂሊንግ" በግርድፉ ሲተረጎም፣ "የክርስቲያን ሳይንሶች ፈውስ በአንድ ምዕተ ዓመት" በሚል ርእስ አዘጋጅቶ እያሠራጨ ባለው መጽሐፍ፣ በክርስቲያን ሳይንሶች የፈውስ ቀመር ተፈወሱ የተባሉትን ግለሰቦች፣ "ምስክርነት" አቅርቦአል[40]።

"የሕዝቦች ቤተ መቅደስ" (ፒፕልስ ቴምፕል) የተባለው መናፍቃዊ ድርጅት መሥራች የሆነው ጂም ጆንስ፣ ከ40 የሚበልጡ ሰዎችን ከሙታን እንዳስነሣ ይገልጻል[41]። ጆንስ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኘው የመኪኖች ማቆሚያ ላይ ተኩስ እንደ ተከፈተበት፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የነበሩትም ሰዎች ተኩሱን እንደ ሰሙ፣ ከዚያም በደም የተጨማለቀና ሁለት ቀዳዳ ያለበት ሸሚዝ በእጁ ይዞ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ለነበሩት ሰዎች፣ ሁለት ጊዜ በጥይት ተመትቶ ከሞተ በኋላ ራሱን ከሞት እንዳስነሣ ገልጾአል[42]። ከጆንስ ጋር በእዚያ የነበሩ ሰዎች ራሳቸው፣ ባደረጉት

[40] *Gomes* ገጽ *39* ላይ ከ*A Century of Christian Science Healing* (*Boston: Christian Science publishing Society, 1966*) ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[41] *Gomes* ገጽ *39* ከ*Sparks, The Mindbenders*, ገጽ 264-265 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[42] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ *39*።

ይህ ማስተባበያ አዋጪ ብቻ ሳይሆን፣ ስሕተት መሆኑንም ቢቢሲ በስፋት ተሳልቆበታል። የሚያሳዝነው ግን፣ ግለሰቡ ትክክል ሊሆኑ ያልታዩ ትንቢቶችን በርካታ ጊዜ እንደ ተናገረ፣ የመገናኛ ብዙኃን ገልጸዋል (ለምሳሌ የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ የእግር ኳስ ጨዋታን በተመለከተ ያስተላለፈው "ትንቢት" ሊይዝለት አልቻለም፤ ለመሆኑ ግን፣ የእግር ኳስ ጨዋታን በተመለከተ ትንቢት የሚያመጣው አምላክ ምን ዐይነት ነው? ይህስ ሁኔታ ሰዎችን ወደ ድነት ወይም ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዴት ሊያመጣቸው ይችላል?)። ዛሬም ግን በርካታ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ እጅግ ብዙ ሰዎች፣ ግለሰቡ ትክክለኛ ነቢይ ነው የሚል አቋም አላቸው። እንዲያውም ከሁለት ዓመት በፊት፣ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ባርኮቱን ይስጠን፣ ችግራችንን ይፍታልን የሚሉ ሰዎች ጥያቄ አቅርበው፣ አብያተ ክርስቲያንንና አገልጋዮችን ብዙ እንዳሚገተ የምንረሳው አይደለም። የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት፣ ይህን ሰው ለመጋበዝ ቍርጥ ውሳኔ ከማድረጉ የተነሣ፣ የኅብረቱ አባል የሆነችው የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን፣ "ይህ ሰው ተጋብዞ የሚመጣ ከሆነ፣ ከኅብረቱ ጋር ያለኝን አባልነት አቋርጣለው" የሚል ማስጠንቀቂያ በመስጠቷ የግለሰቡ ግብዣ እንደ ተሰረዘ ውስጥ ዐዋቂ ምንጮች ይገልጻሉ።

በዚህ በአሜሪካን አገር የሚኖሩ ኤልያስ አብጤ የተባሉ አባይ ነባይ፣ የባልንጀራቸውን (እንዲያውም "መንፈሳዊ አባቱ ነኝ" የሚሏቸውን) የእስራኤል ዳንሳ ትንቢት (ማለትም ነባዮች በኢትዮጵያ ጋርሳማ በመግባት በአገሪቱ ዕጣ ፈንታ ላይ ይወስናሉ የሚለውን ትንቢት) ለምን አልተፈጸመም የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ የሰጠው ማብራሪያ፣ ልክ እንደ ቲ.ቢ. ጆሽዋ ይህን ማብራሪያ ለመሸከም፣ "መንፈሳዊ ዐቅማችሁ አይፈቅድም፤ እርሱን መመርመር የምችለው እኔ ብቻ ነኝ፤ ምክንያቱም እኔ ለባተኛው ከፍታ ላይ ደርሻለሁ" ብለውናል።



በመሠረቱ "በአፍቅሮተ ነባይ" የተለከፈን ሰው፣ በቃሉ ሥልጣናዊነት ታምኖ መጽሐፍ ቅዱስን መመሪያው አድርጎ መኖር እጅግ እንደሚከብደው ከላይ በስፋት ሞግቻለሁ። ማንን ላግባ፣ ወደ ፊት ኮሌጅ ገብቼ ምን ዐይነት ትምህርት ላጥና፣ ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ራሴን መለየት አለብኝ ወይስ የለብኝም ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን በተመለከተ፣ ቃለ እግዚአብሔርንና የበሳል ሰዎችን ምክር እንዲሁም ጸሎት እንጂ፣ ትንቢት መመሪያ ማድረግ እንደማይገባ በዚህ አጋጣሚ በግልጽ መናገር እፈልጋለሁ።

"ጌታ እገሊትን ለጥቶሃል፤ አግባት"፣ "አምላክ ሥራሽን ትተሽ እንድታገለግዪው ይፈልጋል" ወዘተ የሚለውን ትንቢት ሰምተው የማታ ማታ ቀኑ የጨለመባቸው፣ ከፍተኛ ተስፋ መቍረጥ ውስጥ የወደቁ እጅግ በርካታ ሰዎችን አውቃለሁ። ወገኖቼ የአባይ ነባዮች ትንቢት በጅማም ሆነ በእያንዳንዱ ምዕመን ሕይወት ውስጥ ያመጣው ውድመት እንዲህ በቀላሉ ተነግሮ፣ ተዘክሮ የሚያልቅ እንዳይደለ በግልጽ ሊታወቅ ይገባል። የሠላሳ ሁለት ዓመት የክርስትና ሕይወቴ እንዲሁም የሃያ አምስት ዓመት የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ቆይታዬ በዚህ ረገድ ያስተማረኝ ትምህርት እጅግ የትዬለሌ ነው። የብዙ ሰዎችን እንባና ጸጸት አይቻለሁ። ይህን የምልበት ቀዳማይ ምክንያት ነባዮቹን ለማሳጣት ሳይሆን (ቀድሞውንስ በእኩይ ምግባራቸው የሚጸጸቱ ሰዎች መች ሆኑና?)፣ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርግ የመግለጽ ክርስቲያናዊ ኀላፊነት አለብኝ ከሚለው ጽኑ እምነቴ የመነጨ ምክር ነው። ወገን የሚሊዮኖች እንባና ለቄቃ ትምህርት ሊሆነን ይገባል። በምድር ላይ ለመኖር የተሰጠንን ምጥን ሕይወት፣ የጸጸትና የቍጭት ማላ ልናደርጋት አይገባም። ባወጣው ያውጣው እየተባለ የሚጠለዘው የአባይ ነባዮች ትንቢት፣ ክቡር ሕይወታችን መበላሸት የለበትም። እነርሱ ያሻቸውን ብለው ያለአንዳች ጸጸት ይኖራሉ፤

ይብላኝ ትንቢታቸው ትክክል ነው በሚል፣ የሕይወቱን ቢጋር በዚያ እንጻር ለሚያደራጀው ምስኪን።

## አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" የአርማጌዶን ጦርነት 1914 ከዚያም 1915 ከዚያም 1918 በኋላም 1975 ዓ.ም ይሆናል ብለው ነበር[47]። "የይሖዋ ምስክሮች" ከዐሥራ አራት የማይበልጡ ይህን መሰል ትንቢቶች አስተላልፈዋል[48]። ነገር ግን አንዱም እውነት ሆኖ አልታየም።

"የዳዊት ሥር" *(Branch Davidians)* የሚባለውን መናፍቃዊ ድርጅት የመሠረተውና ከእርሱ ሞት በኋላ የድርጅቱ ነቢዪት የሆነችው ፍሎረንስ የምትባለው ባለቤቱ፣ ሚያዝያ 22 ቀን 1959 ዓ.ም በራእይ 11 ላይ የተጠቀሰው የ1260 ቀናት መጠናቀቂያና ሕዝቅኤል 9 ላይ የተጠቀሰው የፍርድ ቀን መጀመሪያ ይሆናል ብላ ነበር[49]። ከፍሎረንስ ትንቢት የተነሣ ከ1000 የሚበልጡ የድርጅቱ አባላት ያላቸውን ሸጠው፣ ገንዘባቸውን ለቤተ ክርስቲያን ከሰጡ በኋላ፣ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ተሰብስበው ነበር[50] (ትንቢቱ እውነት የሚሆን ከሆነ፣ ገንዘቡን ለቤተ ክርስቲያኒቱ መስጠት ምን ፋይዳ አለው? ዓለም ፍጻሜ ካገኘች በኋላም ገንዘብ ፋይዳ አለው ማለት ነው?)። ኋላ ትንቢቱ ስሕተት እንደ ነበረ የተገነዘቡ በርካታ ሰዎች ድርጅቱን ለቀው ወጥተዋል።

የሕዝቦች ቤተ መቅደስ የሚባለውን ድርጅት የቈረቈረው ጂሚ ጆንስ፣ ኢንዲያና ፖሊስ በተባለችው ከተማ ሐምሌ 15 ቀን 1967 ዓ.ም በኒዩክሊየር ጦርነት ያጠፋል የሚል ትንቢት ተንብዮ ነበር[51]።

[47] ተስፋዬ ሮበሌ፣ *አርዮሳውያን*።

[48] *McDowell and Stewart, The Deceiver ገጽ 26-27*።

[49] *Gomes ገጽ 40 CRI "The Branch Davidians, Statement Number DD-025" prepared by Richard Abanes (11 March 1993) ገጽ 2* ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[50] ዝኒ ከማሁ።



የእግዚአብሔር ልጆች *(Children of God)* የሚባለውን መናፍቃዊ ድርጅት ያስተዳድር የነበረው ሞሰስ ዴቪዲ፣ ከሆቴክ የሚባል ጅራታማ ኮከብ በ1974 ዓ.ም አሜሪካንን ያጠፋል የሚል ትንቢት ተንብዮ ነበር[52]።

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን ውስጥ የፈሉት አባይ ነባዮች ብዙ ውድመት ሲያደርሱ አይቻለሁ። በውል የማያውቋትን ልጅ አግባ የተባሉ፣ ተፈውሳችኋል ተብለው ከበሽታቸው ጋር የሚኖሩ፣ እንዲያውም አንዳንዶች በተያዙበት በሽታ ያሸለቡ፣ ለአገልግሎት ውጣ የሚለውን የአባይ ነባይ ጥሪ ሰምተው ሥራቸውን በመልቀቅ ከፍተኛ እንግልት የደረሰባቸው፣ አባይ ነባይ ካደረሰባቸው ማታለል የተነሣ ጌታንም ሆነ ክርስትናን ተሰናብተው የሄዱ፣ ዛሬ ላይ ቆመው አባይ ነባዩን፣ "እግዚአብሔር ይይለት ሕይወቱን አበላሸ" የሚሉ እጅግ በርካታ ሰዎችን አውቃለሁ።

ጌታ የራሳችንን ጉዳይ በመጀመሪያ በግልጽ የሚናገረው ለእኛ ለባለጉዳዮቹ ነው። ቋሚ የሆነ ፍላጎት በእኛ ውስጥ በማኖር፣ ይህንኑ ጉዳይ ጌታ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለባልንጀሮቻችን፣ ለቤተሰቦቻችን፣ ለመጋቢዎቻችን፣ ለተለያዩ አገልጋዮች ወዘተ በመናገር ጉዳዩን ያስረግጥልናል። ጌታ በአገር በዘመድ የሌለ እንግዳ ነገር ዱብ አያደርግም። በጊዜያዊ መነሣሣትም ቋሚ ሕይወታችንን አያመሳቅልም። ወገኖቼ ይህ ነው ጤናማውና መደበኛው የክርስትና ሕይወት። ቢያንስ እኔ የገባኝ የክርስትና ሕይወት ይህ ነው።

[51] *Gomes ገጽ 41* ከ*Sparks, The Mindbenders ገጽ* ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[52] ዝኒ ከማሁ። *Moses David, "40 Days and Nineveh Shall Be Destroyed" Tract published in 1973.*

## 13. የአማኞችን ክህነት ይክዳሉ

መጽሐፍ ቅዱስ ምዕመናን ሁሉ ካህናት መሆናቸውን ያስተምረናል (1ጴጥ 2፥4-10፤ ራእ 1፥6፤ 5፥10)። ይህም ማለት እያንዳንዱ አማኝ ያለምንም ሰብአዊም ሆነ መንፈሳዊ አካላት (ለምሳሌ መላእክት) መካከለኛነት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ብቻ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘት ይችላል ማለት ነው (ዕብ 4፥16)።

በርካታ አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች ይገዙላቸው ዘንድ አማኝ ሁሉ ካህን ነው፣ አማኝ ከአምላኩ ጋር በቀጥታ መገናኘት ይችላል የሚለውን የአማኞችን ክህነታዊ መብት በመካድ ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት የሚረዱት በእኛ አማካይነት ብቻ ነው ይላሉ (1ዮሐ. 2፥26-27)።

## አስረጅ

"የዳዊት ሥር" በመባል ይታወቅ የነበረው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ መሥራች የነበረው ዴቪድ ክሬሽ፣ ለተከታዮቹ መጽሐፍ ቅዱስን ማብራራት (መተርጐም) የሚችለው እርሱ ብቻ እንደ ሆነ ገልጾአል[53]። "የይሖዋ ምስክሮችን" ድርጅት የመሠረተው ቻርልስ ታዝ ራስል፣ "ስተዲስ ኢን ዘ ስክሪፕቸርስ" በተባለው መጽሐፉ፣ "የተገነዘብነው ነገር ቢኖር፣ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ አንብበው መለኮታዊ ምሪትን ማግኘት እንደማይችሉ ነው። ስተዲስ ኢን ዘ ስክሪፕቸርስ መጠቀም ከጀመረ በኋላ ጥቂት ተጠቅሞባቸው፣ ተረድቶአቸው፣ ለዐሥር ዓመት እንኳ ካነበባቸው በኋላ የሚተዋቸውና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የሚመለስ ሰው፣ ከተሞክሮአችን የተረዳነው ነገር በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ ጨለማ

[53] Gomes ገጽ 41 ከAbanes, ጠቅሶ እንደ ጻፈው።



እንደሚሄድ ነው"[54] ብሎአል። ድርጅቱ እስከ አሁን ድረስ መለኮታዊ እውነትን ለመረዳት፣ ለመጠበቂያ ግንብ ማኅበር መገዛት የግድ አስፈላጊ እንደ ሆነ ይገልጻል[55]።

የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ሙን፣ "ሙሴ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን እውነት የገለጠበት፣ በአዲስ ኪዳን ዘመን ኢየሱስ የእግዚአብሔርን እውነት የገለጠበትና ሁለቱ ኪዳናት የሚቋጩበት (የሚደመደሙበት) የሙን ዘመን"[56] በሚል፣ የሰብአውያን ታሪክ በሦስት ትልልቅ ክፍሎች እንደሚከፈል ያስተምራል። ሙን "መለኮታዊ ሕግጋት" በሚል ርእስ የጻፈው መጽሐፍ፣ "በዘመኑ መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር የዓለማትንና የሕይወትን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መልእክተኛውን ላከ። ስሙም ሰን ሙዮንግ ሙን ይባላል"[57]።

በዙሪያችን የፈሉትም አባይ ነባዮች አምላክ እነርሱን አፍ ለአፍ እንደሚያናግር፣ በእንድ ጉባኤ ሺህ ለማንያ መገለጥ እንሚያወርድላቸው እያየን ነው። ይህ እውነት ከሆነ ጌታ ለራሳችን ጉዳይ ቢያንስ አንድ ጊዜ እንኳ እንዴት ሹክ ሳይለን (ይቀራል በቃሱ በህልም ወዘተ)? ጸጋን መካፈል ክርስቲያናዊ ትምህርት ቢሆንም ክርስቲያኖችን በአንድ ግለሰብ ዙሪያ ማከማቸት፣ አምላክ በቋሚነት የሚናገራችሁ በእኔ አማካይነት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችሁን ለቃችሁ እኔ ወዳለሁበት ወይም እኔ ወደ ቈረቈርሁት ቤተ ክርስቲያን ኑ የሚለው ጥሪ፣ የአማኞችን የክህነት መብት በጽኑ የሚጻረር ነው። በመሠረታዊው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት

[54] Anthony A. Hoekema, The Four Major Cults (Grand Rapids: Eerdmans, 1963) ገጽ 227።
[55] You Can Live Forever in paradise on Earth (1982) ገጽ 191-95። ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 281-283።
[56] Gomes ገጽ 42።
[57] ዝኒ ከማሁ።

ትምህርት፣ ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው የዳኑ ሰዎች በቃሉ ዙሪያ በሚያደርጉት ኅብረት እንጂ በግለሰቦች ማንነት አይደለም።

## 14. ትክክለኛውን የቅዱሳት መጻሕፍት አፈታት መንገድ አይከተሉም

መናፍቃን ትክክለኛ ያልሆነውን አስተምህሮአቸውን የሚያጸኑት፣ ትክክለኛ ያልሆነ የቅዱሳት መጻሕፍትን አፈታት መንገድ በመከተል ነው[58]። አብዛኛውን ጊዜ ይህ እውን የሚሆነው፣ አንድን ክፍል ወይም ጥቅስ ከዐውደ ምንባቡ አላቀው በመተርጐም ነው። ለሰዋሰው አወቃቀሩ፣ ለቃላት አሰካኩ፣ ለክፍሉ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ/ጾታ (ዘወግ)፣ ለዐውደ ምንባቡ፣ ለነገረ መለኮታዊ ፍካሬው አንዳችም ቦታ አይሰጡም። መናፍቃን፣ መናፍቃን የሆኑበት ዋነኛው ምክንያት ይኸው ነው። እንቀበለዋለን የሚሉትን የሥነ አፈታት መርሖ ወጥነት ባለው ሁኔታ እንኳ ሲጠቀሙበት አይታይም።

በአባይ ነባዮች ተዘውትሮ የሚታየው የአፈታት መንገድ፣ ምስጥሮታዊ (ትርጒም ፈልቅቅ ትርጓሜ *alegorization)* የሚባለውን የአተረጓጐም ስልት ነው[59]። ዐውድን መሠረት ያደረገ ትርጓሜ አይመቻቸውም። መጽሐፉ ለተጻፈበት መቼት እንዲሁም ሥነ ጽሑፋዊ ጾታ (ዘውግ) አንዳችም ቊብ የላቸውም። የሚሹትን ነገር ጮኽ ብሎ የሚናገርላቸው እስከ መሰላቸው ድረስ፣ መኸረጥ አድርጎ መውጣቱን ይችሉበታል፤ ባይሆን ጉባኤው የሥነ ትርጓሜአቸውን ሕጸጽ እንዳያስተውል፣ ንግግራቸውን በአልልታና በሆታ ያሳጅባሉ፣

---

[58] ቅዱሳት መጻሕፍትን የምንተረጕመው እንዴት ነው የሚለውን ጉዳይ በግልጽ ለመረዳት ከፈለጉ፣ ወንድም ምኒልክ አስፋው፣ *መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ ሥልቱ* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ እንዲያነቡ እናበረታታለን።
[59] መናፍቃን ቃለ እግዚአብሔርን እንዴት እንደሚያጠናብሩ በትክክል ለማረዳት የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ በተለያዩ መናፍቃን ላይ የጻፋቸውን መጻሕፍት ይመለከቷል።



"የገባው አሜን ይበል"፣ "አጠገብሽ ያለውን ምስጢሩ ገብቶኛል በዪው" በዚህ ረገድ ነባር ስልታቸው ነው።

## 15. ቅይጥነት

ቅይጥነት የሚለውን ቃል የተጠቀምሁት፣ ሁለት የተለያዩ፣ አብዛኛውን ጊዜ ተቃራኒ የሆኑ ነገሮችን አብሮ መቀየጥ ወይም መደባለቅ የሚለውን ትርጒም እንዲይዝልኝ ነው። አብዛኞቹ መናፍቃን የቅይጣዊነት ችግር እንብዛም አይታይባቸውም። ነገር ግን ከሩቅ ምሥራቅ ትምህርት አስተሳሰብ (ከኮንፊሽስና ከቡድሃ እምነት) ጋር የተዳበሉ ትምህርቶች እንዲሁም በዙሪያችን የፈሉት አባይ ነባዮች ይህ ዐይነቱ ችግር በግልጽ ይስተዋልባቸዋል።

## አስረጅ

እንደ "ክርስቲያን ሳይንስ"፣ ብዙ አባይ ነባዮችን የተጣባቸው "የእምነት እንቅስቃሴ" ትምህርት እንዲሁም የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን የቅይጥነት ችግር በሰፋት ይታይባቸዋል። እንደነዚህ መናፍቃን ትምህርት ለማያዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ዕውቀት በስሜት ሕዋሳቶቻችንና በአዕምሮአችን ልንደርስበት አንችልም፤ እንዲያውም በዚህ መልክ የምናውቀውን እውነት ካልኰነንን (ካልካድን) በቀር ወደ ለማያዊው የዕውቀት ደጅ መድረስ (ማግኘት) አንችልም ይላሉ። እንደነዚህ መናፍቃን ትምህርት መንፈሳዊውን እውነት የምንገበየው በመገለጥ ዕውቀት ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ኖስቲሲዝም ከሚባለው የጥንት ኑፋቄ የተቀዳ አረማዊ ትምህርት ነው። በዚህ ረገድ አባይ ነባዮች፣ ክርስቲያን ሳይንስና የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን አንድ ዐይነት አስተሳሰብ ይጋራሉ።

## 16. ከመናፍስቱ ዓለም ጋር መገናኘት ወይም ጥንቆላ

አብዛኞቹ አባይ ነባዮችና መናፍቃን ከመናፍስት ዓለም ጋር የመገናኘት ችሎታ እንዳላቸው ይናገራሉ።

### አስረጅ

ለምሳሌ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚባለውን መናፍቃዊ ድርጅት ይመራ የነበረው ሞስስ ዴቪድ፣ ዛሬ በአፀደ ሥጋ ከሌሉት እንደ ማርቲን ሉተር ካሉ ሰዎች ጋር ይነጋገር እንደ ነበር ገልጾአል[60]።

የዩኒፊኬሽን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው ሙን፣ "ዛሬ በዓለማችን ላይ በርካታ ሰዎች ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር መገናኘት ችለዋል፤ ይህም የሐሥ 2፥17 ፍጻሜ ነው"[61] ባይ ነው። ሙንም ሆነ ባለቤቱ እንዲሁም ተከታዮቹ፣ በጸሎት ጊዜ ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር መገናኘት ይችሉ እንደ ነበር ይገልጻሉ[62]።

የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን መሥራች የነበረው ጆሴፍ ስሚዝ፣ ጠጠር እንደ መጣል ዐይነቱን ጥንቆላ ይከተል እንደ ነበር፣ መጻሕፍት ያስረዳሉ[63]።

ለሞኑን በመገናኛ ብዙኃን የወር ባለተራ የሆነው፣ አባይ ነባይ ኤልያስ አብጤ፣ "በአንድ ጊዜ ሁለት ቦታ መገኘት ካልቻልን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ ነው እንዲሁም ሙታንን ከሞት ማስነሣት ይችላል ማለት አንችልም" ሲል ተደምጧል። ይህ በጥንቆላው ዓለም እውን እንደሚሆን የሚነገርለት ከአካል ወጥቶ መሄድ፣ "አስትራል

60 Gomes ገጽ 44 ከAllan, *Shopping for a God,* ገጽ 149 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

61 ዝኒ ከማሁ ገጽ 44 ከMoon, *Divine Principle* ገጽ 177 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

62 McDowe and Stewart, *The Deceiver,* ገጽ 177 ጠቅሰ እንደ ጻፉት።

63 ለምሳሌ፦— Kurt Ven Gorden, *Mormonoism.* D. Michael Quinn's *Early Mormonism and the Magic World.*



ፕሮጀክሽን" *(Astral Projection)*፣ ለብሉያትም ሆነ ለሐዲሳት እጅግ ባይተዋር ትምህርት ከመሆኑም ባሻገር፣ በርካታ የእምነት አበው፣ ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ አረማዊ ነው ሲሉ ጽፈዋል።

## 17. መናፍቃዊ እንቅስቃሴአቸውን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ አስቀድሞ እንደ ተነበየላቸው ይገልጻሉ

አንዳንድ አባይ ነባዮችና መናፍቃን እነርሱ ከመምጣታቸው በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነርሱ መምጣት አስቀድሞ የምሥራች እንደነገረላቸው ይገልጻሉ። ይህ ከቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት መርሖ ጋር እንዴት እንደሚቃረን መገመት ይቻላል።

### አስረጅ

"የይሖዋ ምስክሮች" በሉቃስ 12፥42 ላይ፣ "ልባምና ታማኝ ባሪያ" የተባለው ቃል የድርጅታችንን የአመራር አካላት የሚያሳይ ትንቢት ነው ባዮች ናቸው።

"የእግዚአብሔር ልጆች" በመባል የሚታወቀው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ አባላት፣ "የእግዚአብሔር ልጆች" *(1ዮሐ. 3፥10፤ 5፥2)* የሚለው ሐረግ በቀጥታ ስለ እነርሱ ድርጅት እንደ ተናገረ ይገልጻሉ[64]።

ጆሴፍ ስሚዝ በዘፍጥረት ምዕራፍ 50 ላይ 14 ቍጥሮችን በመጨመር ስለ እርሱና ስለ ድርጅቱ (የሞርሞን ቤተ ክርስቲያን) የሚናገር ትንቢት እንደ ሆነ ገልጾአል[65]።

"የዳዊት ሥር" የሚባለው መናፍቃዊ እንቅስቃሴ መሥራች ዴቪድ ኮሬሽ፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረው ንጉሥ ዳዊት

64 Gomes ገጽ 45።

65 ዝኒ ከማሁ።

ተምሳሌት *(antitype)* እንደ ነበረ ገልጾአል[66]:: ይህ ብቻ አይደለም ኮሬሽ በኢሳይያስ 45 ላይ የተጠቀሰው የንጉሥ ቂሮስ ተምሳሌት እንደ ሆነም ያስተምር ነበር (በዕብራይስጥ "ቂሮስ" ማለት ኮሬሽ ማለት ነው):: ስለዚህ ዴቪድ ኮሬሽ የሚያደርገው ነገር ሁሉ እንደ ኢሳ. 45÷13 መሠረት በእግዚአብሔር ምሪት ነው[67]:: ኮሬሽ በራእይ 6 ላይ የተጠቀሰው በግ እርሱ እንደ ሆነም ገልጾአል[68]::

ብዙ እባይ ነባዮች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ ልዩ ትኩረት እንደ ሰጠ እየነገሩን ነው። በዚህም ሂደት ውስጥ እነርሱ ከኢትዮጵያ የሚነሣውን የመጸኢ ዘመን ጦር እንደሚቀቡ በመግለጽ ላይ ናቸው። በዚህ ረገድ መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳንና ቄስ በሊና ሳርካ በአስረጅነት የሚጠቀሱ ጎምቱ አበው ናቸው[69]:: እነዚህ ሰዎች በዛሬዩቱ ቤተ ክርስቲያን ላይ እያመጡ ያሉት ውድመት ራሱን የቻለ መጽሐፍ የሚወጣው ነው። መጋቢ በቀለ ወልደ ኪዳን በተለያየ ጊዜ እያሠራጫቸው ያሉ ትምህርቶች እንዲሁም ቄስ በሊና ሳርካ በየቦታው እየሄዱ የሚተነብዩት ትንቢትና የሚያፈሱት ዘይት ከምንገምተው በላይ ትልቅ ጉዳት እያመጣ ነው። በዚህ ረገድ

---

[66] ዝኒ. ከማሁ።

[67] ዝኒ. ከማሁ። ከ*Abanes, "The branch Davidians"* ገጽ 4 ጠቅሶ እንደ ጻፈው።

[68] ዝኒ. ከማሁ።

[69] ጋሼ በቀለ ወልደ ኪዳን በዚህ መጠን መስመር ስቶ መውጣቱ፣ በዚህም መጠን የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ በሚጐዳ ተግባር ላይ በመሠማራት የአባይ ነባዮች አፈ ቀላጤና ዐቅብተ ነባይ ሆኖ ብቅ ማለቱ አስደንቆናል። "መጨረሻችንን..አንተው አብጅልን" የሚለው የጥንት ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች መዝሙር ትልቅ ትርጉም ይዞ የሚከሠተው በዚህ ዐይነቱ ገጠመኝ ውስጥ ነው። ጋሼ በቂ የቀድሞ ድካምህን እናደንቃለን፤ በአንጻሩ ደግሞ አሁን ያለህበት ጉዳና በተለይ ደግሞ አባይ ነባዮችን ግብር ለማጽደቅ የምትሄድበት አካሄድ ፍጹም ስሕተት መሆኑን መግለጽ እንወዳለን። እንድትመለስም እንጸልያለን።



ወንድም ዘላለም መንግሥቱ በተለያዩ ጊዜያት በእነዚህ ግለሰቦች ላይ ያዘጋጀውን ጽሑፍ እንድታነቡ አበረታታለሁ[70]::

## 18. ለደቃቅ አስተምህሮዎች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት

እባይ ነባዮችና መናፍቃን ዐበይት ከሆኑት የክርስትና ትምህርቶች ይልቅ ለጥቃቅን አስተምህሮዎች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። ለምሳሌ ለአለባበስ፣ ለአምልኮ ቀናት፣ ለክብረ በዓላት፣ ለባንዲራ ለላምታ ስለመስጠት፣ ስለልደት ቀናት ወዘተ።

### አስረጅ

መቼም በዚህ ዘመን እንደ እባይ ነባይ የሚለብስ፣ በሥልት ጠጕሩን የሚቈረጥ የውበት ተወዳዳሪም ሆነ የልብስ አስተዋዋቂ ያለ አይመስለኝም። ቆንጆ ሆኖ መታየት አግባብ ነው፤ ነገር ግን ይህ ሁሉ ለምን አስፈለገ ለሚለው ብዙዎቹ የሚመልሱት ምላሽ፣ "የምለብሰው ለቅባቱ ክብር ነው" የሚል ነው። ይህ የተሳሳተ አሳብን የሚያጸድቅ ብቻ ሳይሆን፣ ንዑስ ትምህርትን ዐቢይ የሚያደርግ ነው። ይህ ደግሞ ራሳቸውን በገበያው ላይ ጥሩ ተወዳዳሪ አድርጎ አቅርቧቸዋል።

በየንግግራቸው ጣልቃ፣ "እጠገበህ ያለውን እንዲህ በለው" የሚለው፣ እንዲያው ጉባኤ ማድመቂያ ሳይሆን፣ "የእሱታዊ ንግግር

---

[70] ጌታ ቢፈቅድና ዕድሜውንና ጤናውን ቢሰጠኝ፣ "የውስጥ ቦርቧሪ" በምላቸው የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አስተማሪዎች ላይ፣ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ለማዘጋጀት ወጥኛለሁ። ምናልባትም ዛሬ እንደ፣ "ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"፣ እንደ "ይሖዋ ምስክሮች" ዐይነቶቹ "የውጭ ወራሪዎች" ይልቅ፣ ትልቅ ጉዳት በማስከተል ላይ የሚገኙት የውስጥ ቦርቧሪዎቻችን ናቸው። አሁን ብዕራችንን ወደ እነዚህ ሰዎች ማነጣጠር ያስበት አይመስላችሁም?

ኀይል” ከሚለው የእምነት እንቅስቃሴ አስተምህሮ የተቀዳ ነው። ካልተናገርህ/ካላወጅህ አታገኝም።

“የይሖዋ ምስክሮች” ባንዲራን መሳለም ውጉዝ ነው፤ የሕዝብም ሆነ ሃይማኖታዊ በዓላትን ማክበር ጣዖትን ማምለክ ነው፤ የሚለው ትምህርታቸው ስሕተት መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ለደቂቃን ትምህርቶች እጅግ ከፍተኛ ትልቅ ትኩረት ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው።

## ማጠቃለያ

ከላይ ለመጠቆም እንደ ሞከርነው፣ ከፀሓይ በታች ያሉትን አባይ ነባዮችና መናፍቃን ሁሉ፣ አጥንተንም ሆነ መርምረን አንዘልቅም—ያን ያህል ጊዜም ሆነ ዐቅም ሊኖረን አይችልም። በየጊዜው ደግሞ አዳዲስ አቀራረቦችና አስተምህሮዎች እንደሚቀፈቀፉ አያጠራጥርም። ስለዚህ መናፍቃን አዘውትረው የሚጥሷቸውን መሠረታውያን ትምህርቶችና አቀራረቦች ጠንቅቆ ማወቅ፣ ግብራቸውንም ሆነ አስተምህሮአቸውን በቀላሉ ለመለየት ትልግ ዕገዛ አለው።

እነዚህ ዐሥራ ስምንት ነጥቦች በየጊዜው የሚነሡትንና አሁንም ያሉትን አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ አስተምህሮአቸውን የመመዘኛ መስፈርት አድርገን ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ጥሩ ትምህርት እውነትን ከውሸት፣ ሠናዩን ከእኩይ የሚለይ ብቻ ሳይሆን፣ የምንለይበትንም መስፈርት የሚሰጠን ነው። በዚህ አንጻር እነዚህ ዐሥራ ስምንት ነጥቦች ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው።



# ክፍል ዐሥር

## “በኢየሱስ ክርስቶስ ስም” ማለት ምን ማለት ነው?



በዚህ በአሜሪካን አገር፣ በማኅበር የሚካሄድ ምህላ (የማኅበር ጸሎት) በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መቅረብ የለበትም የሚል፣ የጦፈ ክርክር ይካሄድ ነበር—በተወሰነ ደረጃም እንኳ ቢሆን፣ ውዝግቡ እስከ ዛሬዋ ቀን የቀጠለ ይመስለኛል። በቤተ ክርስቲያንና በነገረ መለኮት ተቋማት አካባቢ ብዙ ያወያየው ግን፣ “በርግጥ በክርስቶስ ስም መጸለይ ማለት ምን ማለት ነው?” የሚለው መሠረታዊ ነጥብ ነው።

የክርክሩ መነሻ የኖርዝ ካሮላይና ስቴት ስለነበርች፣ በርእስ ጉዳዩ ዙሪያ የዱክ ዩኒቨርስቲ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ቃለ መጠይቅ ተደርጓላቸው እንደ ነበር አስታውሳለሁ። "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጸለይ ማለት በጸሎታችን ማጠናቀቂያ ላይ፣ 'በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ' ብሎ ጸሎትን ማላረግ አይደለም" የሚል አስተያየት ሰጥተው ነበር። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ "አብ በወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፤ ማንኛውንም ነገር በስሜ ብትለምኑኝ እኔ አደርገዋለሁ" (ዮሐንስ 14፥13-14) ብሎ ባስተማረበት ዐውድ፣ የእነዚህ ምሁራን አስተያየት እንዴት ይተነተናል? በርግጥ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" መጸለይ ማለት ምን ማለት ነው?

በቅርቡ ኢትዮጵያውያኑን አባይ ነባዮች፣ የነገረ መለኮት ድጋፍ እሰጣለሁ እንዲሁም ነባዮቹ መንፈሳዊ አባታችን ነህ የሚሉት ሰው፣ የነባዮቹ ተኣምራት እውነተኛ የአምላክ አስተርእዮ ነው፣ ለሚለው ሙግቱ እንደ ዋነኛ መከራከሪያ ነጥብ አድርጎ ያቀረበው፣ "ተኣምራቶቹ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሲጠራ እውን የሚሆኑ ስለሆኑ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ከሌላ ባዕድ መንፈስ ጣልቃ ገብነት የተገኙ ናቸው ማለት በጭራሽ አይቻልም" ሊል ክርክር ገጥሞአል። ይኸውም ስሙ ተጠርቶ የተከወነ ተኣምር ስለሆነ፣ ከስሙ ጀርባ እርሱ መኖሩን፣ የተኣምራቱም ባለቤት እርሱ ራሱ መሆኑን መጠራጠር የለብንም ማለቱ ነው።

በርግጥ፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" መጸለይ ማለት ወይም "የክርስቶስን ስም መጥራት" ማለት ምን ማለት ነው? ይህ መሠረታዊ ነጥብ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮችና ምዕመናን ዘንድ ትክክለኛ ቦታውን የያዘ አይመስለኝም። ይህም ሁኔታ በብዙ ረገድ ለመታለል ያጋለጠን ይመስላል። ይህ ክፍል



በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንዲካተት የተደረገው በዚህ አግባብ ነው። እንግዲያው፣ "በርግጥ የአምላክን ስም መጥራት (ስሙን ማክበር፣ ማወደስ፣ ማግነን፣ ለስሙ መስገድ ወዘተረፈ) ማለት ምን ማለት ነው?" የሚለውን ጉዳይ ለመመርመር ሙከራ እናደርጋለን[1]።

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ ግን፣ በማቴቴስ መጽሔት ቍጥር 14 ላይ፣ "ስሙን መልሱልን" በሚል ርእስ የወጣው መጣጥፍ ነው፤ ይህ መጣጥፍ ለዚህ ጽሑፍ መነሻ ይሁን እንጂ መድረሻ ግን አይደለም—መነሻው ማቴቴስ መድረሻው ደግሞ አባይ ነባዮች ናቸው። የጸሓፊው የወንድማችን ሰሎሞን አበበ ገብረ መድኀን ሙግትና ሒስ ያነጣጠረው፣ በአምላክ ስም አጠቃቀም ላይ ነው—በንግግርም ሆነ በክትበት። ጸሓፊው ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እግዚአብሔር የሚለውን ስም፣ "እግ/ር"፣ "እ/ር"፣ "እግ."፣ "እግዚ" በሚል ምኅጻር አሳጥሮ መጻፉ፣ ተገቢ ያለመሆኑን ይሞግታል።

እንዲሁም አጋንንትን ለመቃወም፣ "በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" በማለት ፈንታ፣ "ቱ! ቱ!"፣ "ቱም! ቱም!"፣ "እ...ስ...ስ...ስ...ም" ማለት ትርጒም የለሽ ቱማታ እንጂ፣ አንዳችም የቅዱሳት መጻሕፍት ድጋፍ የለውም፤ እንዲያውም ይህ ዐይነቱ አካሄድ ለበቀልንበት ማኅበረሰብና ላደግንበት ባህል ፍጹም ባይተዋር ከመሆኑ ባሻገር፣ ጸያፍነቱ እንደሚበረታ ወንድም ሰሎሞን በስፋት ይሞግታል። በጽሑፉ ሊያስተላልፈው በፈለገው መሠረተ ሐሳብ ላይ መቶ በመቶ ተስማምቻለሁ—በርግጥም የወንድማችን ጽሑፍ፣ ትክክለኛና ወቅታዊ ጽሑፍ ነው! ወገኖቼ እባካችሁ[2] በዚህ

[1] ይህን ሐሳብ በወረቀት ላይ እንዳሰፍር ያበረታታኝ እንዲሁም የመጀመሪያ ረቂቆቹን በማንበብ፣ ብዙ ማጐላበቻ ሐሳቦችን እንድጨምር ያበረታታኝን መጋቢ ዮሐንስ መሐመድን ከልብ አመሰግናለሁ፤ ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ!

[2] በተግሣጹና በቃል አራርሆው ውስጥ አንባብያኑን ብቻ ሳይሆን፣ ራሴንም መክተት ፈልጌ ነው። "እባክህ"፣ "እባክሽ"፣ "እባክዎ" የሚለው ሁለተኛ መደብ እንጂ፣

ረገድ ልንታረም ይገባናል እላለሁ። በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ግን ከወንድሜ የተለየ አሳብ አለኝ። በተወሰነ ደራጃም ቢሆን፣ ይህ ልዩነት የዚህ ጽሑፍ ማዕከል ነው። በዚህ ጽሑፍ፣ የአምላክን ስም በተመለከተ ልናውቀው የሚገባን መሠረታዊ ነገር ምን እንደ ሆነ፣ እቅጣጫ ጠቋሚ አሳቦችን ለማመላከት እሞክራለሁ።

ወደ እሳቤ ያንደረደረኝም ዘንድ፣ እግዚአብሔር አምላክ ስሙን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀበትን የብሉይ ኪዳን ምንባብ በቀዳሚነት ላንሣ፦

> "ደግሞም እግዚአብሔር ሙሴን የአባቶቻችሁ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ወደ እናንተ ልኮኛል፤ ስሜም ለዘላለም ይኸው ነው፤ ወደ ፊት በተከታታይ በሚነሣው ትውልድ ሁሉ የምታስበው በዚህ ስም ነው ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው" (ዘፀአት 3፥15)።

በዚህ ዐውደ ምንባብ ውስጥ አምላክ ስሙን እንዳስተዋወቀ እንዲሁም እግዚአብሔር ከትውልድ ወደ ትውልድ ሁሉ የሚዘከረው (የሚታሰበው) በዚህ ስም እንደ ሆነ ይገልጻል። በዚህ ስፍራ የተገለጠው የእግዚአብሔር የተጸውዖ ስም፣ "ያህዌ" (יהוה) የሚሰው ስም እንደ ሆነ ልብ ይሏል። ይህ ስም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

---

አንደኛ መደብ ብዙ ቍጥርን ማለትም "እኛን" ለማመልከት "እባካችን" እንዲሁም አንደኛ መደብ ነጠላ ቍጥርን ማለትም "እኔን" ለማመልከት "እባኬ" የሚሉ ቃላት በአማኞችን ውስጥ የሉም። በዚህ መልክ በማላመድ ቤተኛ ብናደርጋቸው፣ ለቃላትና ለሰዋስው መዳበር እንዲሁም አሳብን በእቅጩ ለመናገር ዕገዛ የሚያደርጉ ይመስለኛል።



ውስጥ 6,828 ጊዜ የምናገኘው ሲሆን፣ በመዝሙር መጽሐፍ ላይ ብቻ እንኳ 700 ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ጥቅም ላይ ውሏል[3]።

እንዲያውም እኛ ባለንበት የታሪክ ዘመን፣ የዚህ የአምላክ ስም ትክክለኛ ንበት የቱ እንደ ሆነ (እንዴት እንደሚነበብ) የትኛውም የእምነት ተቋም ወይም የትኛውም ሰው በርግጠኝነት አያውቅም። ይህ ስም በአንዳች ግለሰብ ወይም የሃይማኖት ተቋም ያልታወቀበትን ዐቢይ ምክንያት ምን እንደ ሆነ ማብራሪያው እነሆ፦

ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ፣ የጥንት ዕብራውያን ያህዌ (יהוה–*YHWH*) የሚለውን የእግዚአብሔርን የተጸውዖ ስም[4] መጥራት ስለሚፈሩ፣ ያህዌ በሚለው ስም ፈንታ አዶናይ (אֲדֹנָי–*Adonai*) የሚለውን የወል ስም (አዶናይ ማለት "ጌታ" ማለት ነው)፣

---

[3] ያህዌ በሚለው የአምላክ ስም ላይ እንዲሁም ይህ ጽሑፍ በሚያነሣው ጭብጥ ላይ ለፊ ማብራሪያ ከፈለጉ ተስፋዬ ሮበሌ፤ *አርዮሳውያን፤ የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤* (ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር፤ ሎረንቪል፣ ጆርጂያ፤ 2016 ዓ.ም) ይመለከቷል።

[4] በአማርኛ ሰዋስው ሕያዋንም ሆነ ግዑዛን የሚጠሩበት መጠሪያ ሁሉ "ስም" ይባላል። እንደ ታላቁ የአማርኛ ሰዋስው ምሁር እንደ ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ስም አምስት ዐይነት ምድቦች አሉት። እነርሱም (1) የተጸውዖ ስም፣ (2) የወል ስም፣ (3) የጥቅል ስም፣ (4) የቁሳቁስ ስምና (5) የነገር ስም ናቸው። እኔ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የጠቀስሁት፣ የተጸውዖ ስምና የወልን ስም ብቻ ነው። የተጸውዖ ስም ማለት፣ ሰው ወይም አምላክ የሚጠራበት፣ የግሉ የሆነና እርሱ ብቻ ተለይቶ የሚጠራበት መጠሪያ ማለት ነው። ያህዌ ወይም ኤልሻዳይ የሚሉት ስሞች የአምላክ የተጸውዖ ስም ናቸው። የወል ስም ግን ዐይነቱ አንድ የሆነ ነገር ሁሉ የሚጠሩበት የጋራ መጠሪያ ነው። በዕብራይስጥ አዶናይ የሚለው ስም፣ በአማርኛችን "ጌታ" ማለት ስለሆነ፣ በወል ስም ፈርጅ ውስጥ ይመደባል። በግሪክ ደግሞ "ቴዎስ" እና "ኩሪዮስ" የሚሉት ስሞች እንደ ቅደም ተከተላቸው እግዚአብሔርና ጌታ የሚል ትርጉም ስላላቸው፣ በወል ስም ውስጥ ይካተታሉ።

ያህዌ በሚለው ስም ምትክ ተክተው ይጽፉ እንዲሁም ይናገሩ ነበር። ይህን የአምላክ ስም መጥራት እንዲፈሩ ያደረጋቸው ዋነኛ ምክንያት፣ "የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ" የሚለው፣ ከዐሥርቱ ትእዛዛት መኻል ሦስተኛውን ሕግ በተሳሳተ መንገድ በመረዳታቸው ነው። ይኸውም ተሳስተን ባልሆነ መንገድ ስሙን ጠርተነው ከሆነ፣ ቅሥፈት ያጋጥመናል የሚል ፍርሓት። ይህ ብቻ አልነበረም፣ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ያባዙ የነበሩት ጸሓፍት (እንዳሁኑ የማተሚያ መሣሪያ በወቅቱ ስላልነበር) ያህዌ የሚለው የአምላክ ስም በሚገኝበት ቦታ ሁሉ፣ እጃቸውን በሣሙና ሙልጭ አድርገው ይታጠቡ እንዲሁም ብዕራቸውን በንጹሕ ውሃ ያሰቀልቁ ነበር። ይህ ማለት ደግሞ፣ አንድ ጸሓፊ ብሉያትን ገልብጦ እስኪጨርስ ድረስ ወደ ሰባት ሺህ ጊዜ ያህል እጁንና ብዕሩን በዚህ መልክ ያጸዳ ነበር ማለት ነው። ይህ ሁሉ ድካም የአምላክን ስም በከንቱ ላለመጥራት እንዲሁም ለስሙ የሚገባውን ትልቅ ክብር ለመግለጽ ነው። ስለዚህ የአምላክህ የእግዚአብሔር ስም በከንቱ አትጥራ የሚለውን ሕግ ላለማፍረስ በሚያደርጉት ትንቅንቅ/ጥንቃቄ፣ ያህዌ የሚለውን የተጸውዖ ስም ከመጠቀም ይልቅ፣ አዶናይ የሚለውን የወል ስም ተክተው በመጠቀም ጀመሩ። በዚህም መንገድ ያህዌ የሚለውን ስም ከሃይማኖት ሥርዐታቸው ውስጥ አስወጡ።

የጥንት ዕብራውያን ድምፅ ተቀባይ ፊደላትን *(consonants)* ብቻ በመጻፍ፣ በሚያነቡበት ጊዜ ብቻ ድምፅ ሰጪ ፊደላትን *(vowels)* እያስገቡ ጽሑፋቸውን ያነቡ ነበር። በስድስተኛውና በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ፣ የዕብራይስጥ ቋንቋ እያደገ ስለመጣ፣ ድምፅ ተቀባይ ፊደላትን ከድምፅ ሰጪ ፊደላት ጋር አስባጥሮ መጻፍ ተጀመረ። ማሶራውያን *(Masoretes)* የሚባሉት የዕብራይስጥ ቋንቋ ሊቃውንት፣ ለዕብራይስጥ ፊደላት አናባቢ ምልክቶችን በመፍጠር፣



እነዚህን ምልክቶች ከተናባቢ ሆህያት ጋር አቀናጅተው መጻፍ ሲጀምሩ፣ ያህዌ ለሚለው ስም ግን አናባቢ ሳያበጁለት ቀሩ— ምክንያቱም ያህዌ የሚለው ስም ባለባቸው ቦታዎች ሁሉ፣ "አዶናይ" (אֲדֹנָי) የሚለውን ስም ተክቶ የመናገር ጠንካራ ልማድ ነበረና፣ ለዚህ ስም አናባቢ ማበጀት አላስፈለጋቸውም[5]። "ልማድ ሲሰለጥን ቀኖና ይሆናል" ይሏል ይኸው ነው። ይህ አናባቢ ያልተበጀለት ያህዌ የሚለው ስም ድምፅ ተቀባይ ፊደላት— יהוה—*YHWH* ቴትራግራሞቶን በመባል ይታወቃል።

ነገር ግን አይሁዶች ያህዌ የሚለውን ስም እግዚአብሔርን ከመፍራትና ስሙን ከማክበር የተነሣ ስለማይጠሩት፣ ቋንቋው ሲያድግ የቀድሞውን ትክክለኛ አነባበብ አዲሱ ትውልድ ሳያውቀው ቀረ። ይህን ችግር ለመፍታት ዕብራውያን አዶናይ (אֲדֹנָי—*Adonai*) በሚለው የአምላክ ስም ላይ የሚገኙትን ድምፅ ሰጪ ሆህያት ማለትም *"a, o, a"* ያህዌ በሚለው ድምፅ ተቀባይ ፊደላት (ቴትራግራማቶን) ውስጥ በመጨመር፣ *YaHoWaH* ወይም

[5] ይህ ለዕብራይስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ለአብዛኞቹ ጥንታውያን ቋንቋዎች እውነት የሆነ ክሥተት ይመስላል። ለምሳሌ የግእዝ ቋንቋ አናባቢ ሆህያት የተቀመሩለት ከጊዜ በኋላ እንደ ሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ቀሲስ ዶክተር ምክረ ሥላሴ ገ/አማኑኤል፣ *"በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በግእዝ ቋንቋ"* በሚል ርእስ አዘጋጅተው ያሳተሙት መጽሐፍ ይህን ጉዳይ በተመለከተ እንዲህ ይላል፣ "በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በቅዱስ ፍሬምናጦስ (አባ ሰላማ) ጊዜና ከአብርሃ ወአጽብሐ ዘመን ወዲህ ነው፣ እንጂ ከዚያ በፊት ፊደላቱ ቢኖሩም አናባቢ ምልክቶች ሳይኖሩአቸው የነበረው ግእዙ ፊደል ብቻ በመሆኑ ፊደሎቹ ስላስቸገሯቸው ለካዕብ፣ ለሣልስ፣ ለራብዕ፣ ለሐምስ፣ ለሳድስና ለሳብዕ የሚሆኑ የፊደላቱን ድምፆች የሚለዋወጡ አናባቢ ምልክቶችን ጨምረው እያንዳንዱ ፊደል ሰባት ዐይነቶች እንዲሆኑ አዘጋጅተው ለአጻጻፍና ለድምፅ አሰባጥ እንዲመች አድርገውልናል" (ገጽ *5*)።

*YaHWaH* ተብሎ እንዲነበብ አደረጉ። ይህ አንግዲህ የማሶራውያኑ ፈጠራ እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

በዚህ ቦታ ልናስተውለው የሚገባን ትልቁ ቍም ነገር፣ ቴትራግራማቶንን ምንም ብለን ማንበብ ያለመቻላችንን ነው። ምክንያቱም የድምፅ ተቀባይ ፊደላት ቅንጅት ብቻ ስለሆነ፤ ለማንበብ ደግሞ ድምፅ ሰጪ ፊደላት የግድ ያስፈልጋሉ። ከዚህ ሐቅ የተነሣም ነው፣ ያህዌ የሚለው ስም ሰው ሠራሽ ስም ነው የሚባለው[6]። ነገር ግን ያህዌ የሚለው ስያሜ ቴትራግራማቶን ሊነበብበት ከሚችልባቸው አጅግ በርካታ አማራጮች መኻል አንዱ መሆኑን ልብ ይሏል[7]።

ከዚህም ይልቅ አስደናቂ የሆነው ክሥተት፣ የቴትራግራማቶን ንበት በትክክል በሚታወቅበት ዘመን፣

[6] "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው "የይሖዋ ምስክሮች" ድርጅት፣ ለው ድነት የሚያገኘው ይህን የአምላክ ስም በመጥራት እንደ ሆነ እንዲሁም በምድር ላይ ይህን ስም ለፍጥረት ሁሉ በማስተዋወቅ ላይ የሚገኘው ይኸው ድርጅት እንደ ሆነ ያስረዳል። በአንጻሩ ደግሞ ይህ የአምላክ ስም ትክክለኛ አነባበብ እንደማይታወቅ፣ አሁን ያሉት አማራጭ አነባበቦች ("ጆሆቫ" ወይም "ያህዌ" የሚሉት ስያሜዎች) ሰው ሠራሽ እንደ ሆኑ ገልጾአል። በዚህ ረገድ ድርጅቱ እያተመ ከሚያወጣቸው ጽሑፎች መኻል የሚከተሉትን ሁለት መጻሕፍት ይመለከቷል—*Aid to Bible Understanding* ገጽ 884-885። *ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር*፤ ገጽ 195። ትክክለኛውን የአምላክ ስም ማወቅ ለድነት እጅግ ወሳኝ ጕዳይ ነው እንዲሁም የአምላክን ስም ለፍጥረት ሁሉ የምናሳውቅ ብቸኛ የምድር ወኪል ነን እየተባለ፣ በአንጻሩ ደግሞ የአምላክ ስም ትክክለኛ ንበት አይታወቅም ማለት ትልቅ ተቃርኖ ነው። እንግዲያው የድርጅቱን ተከታዮች ሊጠየቁ ከሚገባቸው ጥያቄዎች መኻል አንዱ፣ "እንዴት የማይታወቅ ስም ዕወቁ እንባላለን፤ እንዴትስ ሰው ሠራሽ የሆነ ስም ድነት ለማግኘታችን ቅድመ ሁኔታ ሊሆን ይችላል?" የሚለው ነው።

[7] በቴትራግራማቶን ላይ የቀረበው ትንታኔ በአብዛኛው የተወሰደው ጸሓፊው፤ *አርዮሳውያን* በሚል ርእስካዘጋጀው መጽሐፍ ነው።



ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተተረጐመው የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም፣ ይህን ስም አንዳችም ጊዜ እንኳ ያለመጠቀሙ ነው። በዘመነ ብሉይ (ከ300 ዓ.ቅ.ክ[8] እስከ 200 ዓ.ቅ.ክ ባለው ጊዜ) ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ ቋንቋ የተተረጐመው የስብዐ ሊቃናት ትርጕም፣ ያህዌ የሚለውን የእግዚአብሔር የተጸውዖ ስም በጽርዕ (በግሪክ ቋንቋ) "**ቴዎስ**" (θεὸς ማለትም እግዚአብሔር) እንዲሁም "**ኩሪዮስ**" (κύριός ማለትም ጌታ) በሚለው የግሪክ የወል ስያሜ ነው የተረጐመው።

አስደናቂ የሆነው ሌላው ጕዳይ፣ የሐዲስ ኪዳን ጸሓፍት በጽሑፎቻቸው ውስጥ አንድም ጊዜ ይህን የአምላክ የተጸውዖ ስም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ያለመጥቀሳቸው ብቻ ሳይሆን፣ ለትምህርታቸው አማኝነትና ማጕልበቻ ብሉያትን እጅግ በርካታ ጊዜ ሲያጣቅሱ[9]፣ ይህን የአምላክ ስም በሐዲስ ኪዳን በኆረ ጽሑፋት ውስጥ አንድም ጊዜ እንኳ ያለመጥቀሳቸው ነው[10]።

በዚህ ቦታ ልንጠይቀው የሚገባን መሠረታዊ ጥያቄ፣ የሐዲስ ኪዳን ጸሓፍያን ምን ነክቷቸው ነው ይህን ስም በጽሑፋቸው ውስጥ

[8] "ዓ.ቅ.ክ" የሚለው ምኅጻረ ቃል፣ ዓመት ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ወይም ከክርስቶስ ልደት በፊት ማለት እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

[9] የብሉይ ኪዳን 295 ክፍሎች በ352 ሐዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ ተጣቅሰው የሚገኙ ሲሆን፣ እንደዚህ ስሌት 4.4 ከመቶ የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ብሉያት ናቸው ወይም 22.5 የሐዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ አንድ የብሉይ ኪዳን ምንባብ ይገኛል እንደማለት ነው። ስበለጠ መረጃ Roger Nicole, *Revelation and the Bible*, ed. Carl. *F.H. Henry (Grand Rapids: Baker, 1958)*, ገጽ 137-151 ይመለከቷል።

[10] "የይሖዋ ምስክሮች" 237 ጊዜ ያህዌ የሚለውን ስም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የጨመሩ ቢሆንም፣ ለዚህ አድራጐታቸው ግን አንዳችም አጥጋቢ ማስረጃ ማቅረብ አይችሉም። እንዲያውም በሐዲስ ኪዳን ምንባባት ውስጥ ይህን ቃል መጠቀማቸው ስምት፣ "ኢየሱስ አምላክ አይደለም" ወደሚለው አስተምህሮአቸው እንዲሳቡ አድርጓል።

ሳይጠቅሱ ያሰፉት—ቢያንስ አንድ ጊዜ እንኳ ይህን ስም መጥቀስ እንዴት አልቻሉም? ይህ ብቻ አይደለም፣ እግዚአብሔር የተጠራባቸው የብሉይ ኪዳን የተጸውዖ ስሞች በርካታ ቢሆኑም፣ አንዱም ስም ግን በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ጥቅም ላይ ውሎ አይገኝም። በሐዲስ ኪዳን ግሪክ ቋንቋ፣ በአምላክ የወል ስምነት ተደጋግመው የተጠቀሱት ስሞች "ቴዎስ" (θεός—እግዚአብሔር) እንዲሁም "ኩሪዮስ" (κύριός—ጌታ) የሚሉት ስሞች ናቸው። ከዘመነ ክርስትና በፊት፣ እነዚህ ስሞች የግሪክ ጣዖታትን ለማመልከት ጥቅም ላይ ይውሉ የነበሩ ስሞች መሆናቸውን የመስኩ ምሁራን በግልጽ ያስረዳሉ።

በኦሮምኛ "ጎፍታ/ዋቀዮ"፣ በጉራጊኛ "ጐይታ"፣ በሲዳምኛና በጌዴዎኛ "መገኖ"፣ በትግርኛ "አምላክ"፣ በወላይትኛ "ጦሳ"፣ በአማርኛ "እግዚአብሔር" ወዘተ የሚሉት ስሞች፣ የወል ስም መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፣ ለባዕድ አምልኮም ሆነ ለመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ ያላንዳች ጥያቄና ማመንታት ተጠቅመንባቸዋል፤ እየተጠቀምንባቸውም እንገኛለን[11]።

[11] በአንድ ወቅት በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ዋና ጽሕፈት ቤት ውስጥ፣ "አላህ" የሚለውን የዐረብኛ የወል ስም "እግዚአብሔር" በሚለው የአማርኛ የወል ስም ተክተን እንጠቀም ወይስ አንጠቀም የሚል የሁለት ወገን ክርክር ቀርቦ እንደ ነበር አስታውሳለሁ። በእኔ አተያይ ይህ ሙግት ሊፈታ የሚችለው፣ በዚህ ጽሑፍ ጭብጥ ነው የሚል አቋም አለኝ። ክርክሩ በቀረበበትም ወቅት የለጠሁት አስተያየት ይህንኑ የተከተለ ነበር። ይህ ጽሑፍ ግን የኅብረቱ ጽሕፈት ቤት ገብቶበት የነበረውን ውዝግብ ለመፍታ ጥሩ መደላድል የሚያደርግ ይመስለኛል፤ ይኸውም የአምላክን ስም አጠቃቀም በተመለከተ ማለቴ እንጂ፣ ነገረ መለኮት ስያሜዎችን በተመለከተ ግን፣ እያንዳንዱ ስያሜ በተናጠልና በጥሙና መመርመር ያለበት ይመስለኛል። ምክንያቱም የእስልምናና የክርስትና ነገረ መለኮት ዕንሰ አሳቦች እጅግ የተለያየ ፍካሬና እማሬ ስላላቸው።



ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማረው ጸሎት ላይ፣ "ስምህ ይቀደስ በሉ" ወይም "ስሙን ቀድሱ" ተብለን ነበር (ማቴዎስ 6÷9) ታዲያ እንዴት ነው ስሙን ሳናውቅ ስሙን ልንቀድስ የምንችለው? አምላክ በየትውልዱ ሁሉ ለዘላለም እጠራበታለሁ ያለው ስም እንዴት በዚህ መልክ መና ይቀራል? አንዳንድ ለዎች ለዚህ ታሪካዊና ነገረ መለኮታዊ ክሥተት የሚሰጡት ትንታኔ፣ ሐዲስ ኪዳን ከአብ ይልቅ ለወልድ ትልቅ ስፍራ ስለሚሰጥ ጸሓፍያኑ፣ ሆነ ብለው ያደረጉት ነገር ነው የሚል ነው። ይኸውም ሐዲስ ኪዳን፣ "በቃልም ሆነ በተግባር የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት" (ቈላስይስ 3÷17) ይላል። ሁሉን ነገር በጌታ በኢየሱስ ስም ማድረግ ማለት ደግሞ ምን ማለት እንደ ሆነ፣ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሚከተለው መንገድ ያብራራሉ:—

- በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተሰብሰቡ (ማቴዎስ 18÷20፤ 1ቆሮንቶስ 5÷4)።
- በጌታ ስም አጋንትን አውጡ (ሉቃስ 10÷17፤ ሐዋርያት ሥራ 16÷18)።
- በኢየሱስ ስም ንስሓና የኀጢአት ይቅርታ እንዲሁም ድነትን ስበኩ፣ (ሉቃስ 24÷47፤ ሐዋርያት ሥራ 4÷12፤ ዮሐንስ 1÷12፤ ሐዋርያት ሥራ 10÷43፤ 1ዮሐንስ 3÷23፤ 5÷13)።
- ጸሎታችሁን በኢየሱስ ስም አድርሱ (ዮሐንስ 14÷13-14፤ 15÷16፤ 16÷23-24)።
- መንፈስ ቅዱስ የሚላክላችሁ በኢየሱስ ስም ነው (ዮሐንስ 14÷26)።
- በኢየሱስ ስም ሕሙማንን ፈውሱ፤ ሽባውን ተርትሩ (ሐዋርያት ሥራ 3÷16፤ 4÷7-10:30)።

- በሰማይም ሆነ በምድር አቻ የለሌው ስም የኢየሱስ ስም ነው (ኤፌሶን 1÷21፤ ፊልጵስዩስ 2÷9-11)[12]::

ልክ ነው ሐዲስ ኪዳን ለጌታችን ለመድኀኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ትልቅ ቦታ ይሰጣል። እንዲያውም ከስሞች ሁሉ በላይ የሆነ ስም ያለውና ጉልበት ሁሉ የሚንበረከክለት ስም፣ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም አንደ ሆነ ይናገራል (ፊልጵስዩስ 2÷9-11፤ ኤፌሶን 1÷21)።

ነገር ግን የኢየሱስ ስም ታላቅ ስም መሆኑ የአብ የተጸውዖ ስም እንዲጠፋ ምክንያት ሲሆን እንዴት ቻለ? የሚለው ጥያቄ አጅግ መሠረታዊ ጥያቄ ነው። የሚከተሉትን የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ልብ ይሏል:—

- "እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜ ይህ ነው፤ ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም" (ኢሳይያስ 42÷8)።
- "ስሜም ለዘላለም ይኸው ነው፤ ወደ ፊት በተከታታይ በሚነሣው ትውልድ ሁሉ የምታስበው በዚህ ስም ነው ብለህ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው አለው" (ዘፀአት 3÷15)።

እነዚህና እነዚህን መሰል ምንባባት እንዴት ይተነተናሉ የሚለው ጉዳይ፣ አሁንም ቋሚ ጥያቄ ሆኖ ይቀጥላል። ይህን ጥያቄ አጥጋቢ በሆነ መንገድ የሚተነትነው ነገረ መለኮታዊ አንድምታ የሚከተለው ነው።

በጥንት እስራኤላውያን ባህል የተጸውዖ ስም፣ ግብርን (ሥራን)፣ ባሕርይን (ተፈጥሮን) እንዲሁም ሥልጣንን የሚያሳይ ነው። አቢግያ ስለባልዋ እኩይ ምግባርና ጠባየ ብልሹነት ስትናገር፣

[12] ይህ ክፍል በቀጥታ የተወሰደው ተስፋዬ ሮበሌ፤ *አርዮሳውያን፣ የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፤* ላይ ነው።



"ጌታዬ ያን ባለጌ ሰው ናባልን ከቍም ነገር አይቍጠረው፤ ስሙ ራሱ ጅል ማለት ስለሆነ፣ ስውየውም ልክ እንደ ስሙ ነው፤ ጅልነትም አብሮት የኖረ ነው" (1ሳሙኤል 25÷25) ማለቷ ስም ግብርንና ባሕርይን እንደሚያመላክት የሚያስተምር ነው። የጥንት ዕብራውያን ስም የሚያወጡት ግለሰቡ እንዲሆን የሚፈልጉትን አልያም ከታሪካቸው ጋር አገናዝበው ነው። ልክ እንደዚሁ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ስሞች በሙሉ፣ የእግዚአብሔርን ግብር፣ ባሕርይና ሥልጣን የሚያሳዩ ናቸው። በሌላ አነጋገር የአምላክ መለኮታዊ ስሞች የማንነቱ ነጸብራቅ ናቸው። በዚህ ረገድ አንዳንድ አስረጆችን ላቅርብ:—

ኤሎሂም (אֱלֹהִים) ወይም ኤሎዋሃ (אֱלוֹהַּ) የሚለው የወል ስም፣ "አምላክ" ወይም "ጌታ" የሚል ትርጓሜ ሲኖረው፣ ከሌሎች የእምላክ ስሞች ጋር ተጫፍሮ ሲቀርብ፣ በተገናኝ ትርጓሜው የእግዚአብሔርን ባሕርይ ወይም ሥራ ያውጃል፤ ለምሳሌ ኤልኤልዮን (אֵל עֶלְיוֹן) "ልዑል (ምጡቅ) እግዚአብሔር" ማለት ነው (ዘፍጥረት 14÷18:19: 20:22)። ኤልኦላም (אֵל עוֹלָם) "ዘላለማዊ አምላክ" ማለት ነው። ኤልሮኢ (אֵל רֳאִי) "የሚያይ/የሚመለከት እግዚአብሔር" ማለት ነው። እግዚእብሔር ሥሉጥ ሳዕለ ኵሉ ነው፤ ዘላለማዊ ጌታ ነው፤ ችግረኞችን ከነችግራቸው መንጥሮ የሚመለከት አምላክ ነው። ለናሙናነት በቈነጠርኋቸው በእነዚህ ስሞች ውስጥ የምናስተውለው ቍም ነገር ስም ባሕርይን፣ ግብርንና ሥልጣንን አመላካች ስንደቅ እንዲሁም ዐላማ መሆኑን ነው። ለዚህም ነው ብሉያት እግዚአብሔር የተጠራባቸው ስሞች ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይና ሥራ ያትታሉ ያልነው።

በሚከተሉት ምንባባት ውስጥ የእግዚአብሔር ስም ከእግዚአብሔር ባሕርይና ግብር ጋር በተለዋዋጭነት እንዴት እንደ ቀረበ ልብ ይሏል:—

- "አቤቱ ስለዚህ በአሕዛብ ዘንድ አመሰግንሃለሁ፤ ***ለስምህም*** እዘምራለሁ" (*መዝሙር 18÷49*)።
- "ለእግዚአብሔር ተቀኙ፤ ***ለስሙም*** ዘምሩ፤ ወደ ምድረ በዳ ለወጣም መንገድ አድርጉ፤ ***ስሙ*** እግዚአብሔር ነው" (*መዝሙር 68÷4*)።
- "ይህን ፍጥረትህን አስብ፤ ጠላት እግዚአብሔርን ተላገደ፣ ሰነፍ ሕዝብም ***ስሙን*** አስቈጣ" (*መዝሙር 74÷18*)።
- "አቤቱ አምላኬ ሆይ፤ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፤ ለዘላለምም ***ስምህን*** አከብራለሁ" (*መዝሙር 86÷12*)።
- "***ስምህን*** ለወንድሞቼ እነግራለሁ፤ በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ" (*መዝሙር 22÷22*)።
- "***ስምህን*** ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፤ በጉባኤም መካከል ምስጋናህን እዘምራለሁ" (*ዕብራውያን 2÷12*)።

በእነዚህ ምንባባት የእግዚአብሔር ስም ከእግዚአብሔር ባሕርይ፣ ግብርና ሥልጣን ጋር መሳ ለመሳ ተነጻጽሮ ቀርቧል። መዝሙረኛው፣ "ለስሙ ዘምሩ" ወይም "ለስምህ እዘምራለሁ" ወይም ደግሞ "ስምህን አከብራለሁ" ሲል፣ ከእግዚአብሔር በተለየ መልክ ለስምህ ብቻ ማኅሴተ እግዚአብሔር እቆማለሁ እያለ አይደለም። "ሰነፍ ሕዝብ የእግዚአብሔርን ስም አስቈጣ" ማለት፣ ራሱን እግዚአብሔርን አስቈጣ ወይም እግዚአብሔርን አዋረደ ማለት እንጂ፣ ከእግዚአብሔር በተለየ መልኩ ስሙ ብቻውን ይቈጣል፣ ይዋረዳል ወይም ይከብራል ማለት አይደለም።



*ዕብራውያን 2÷12* ላይ ያለው ምንባብ በቀጥታ የተጠቀሰው ከመዝሙር 22÷22 ላይ ነው። መዝሙር 22 ደግሞ ጻድቅ ስለሚገጥመው መከራና በመጻኢው ዘመን ስላለው ተስፋ ይናገራል። ጻድቅ በሚያልፍባቸው መከራዎች ውስጥ ሁሉ ግን፣ የእግዚአብሔር እንደ ራሴነቱ አይዛነፍም። የዕብራውያን ጸሐፊ ከዚህ ጻድቅ ስለሚገጥመው መከራ ከሚናገረው ክፍል ውስጥ፣ ኢየሱስ የእኛን ኵነኔና አበሳ ለመሸከም እንደኛ ሰው መሆን እንዳስፈለገው፣ ይህም የክርስቶስ ኢየሱስ ሰው (ትስጉት/ትስብእት) የመሆን ጉዳይ፣ የአምላክን ስም እንደ ማስተዋወቅ ተደርጎ ተወስዷል።

ልብ እንበል በእነዚህ ምንባባት፣ የአምላክ ስም ያህዌ ነው፤ ይህን ስም ለድነታችሁ ዋስትና ነውና ቋጥራችሁ ያዙት አልተባልንም፤ ወይም ወደዚያ የሚያንደረድር አንዳችም ጠቋሚ አሳብ አልቀረበም። በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ፣ ኢየሱስ የትኛውንም የብሉይ ኪዳን ስመ አምላክ በመጥራት ለደቀ መዛሙርቱ አይናገር እንጂ፣ ኢየሱስ በሕይወቱም ሆነ በሞቱ አባቱን በሚገባ መንገድ ተርኰታል (*ዮሐንስ 1÷18*)። እኛም፣ "ከአባቱ ዘንድ የመጣውንም የአንድያ ልጅን ክብር አይተናል" (*ዮሐንስ 1÷14*)።

ከእነዚህ መረጃዎች በግልጽ የምንረዳው ቊም ነገር፣ የአምላክን የተጸውዖ ስም አላወቅንም ማለት ስሞቹ የሚወክሉትን አምላክ አናውቅም ማለት አይደለም። የተጸውዖ ስሞች ንበት ጠፋብን ማለት፣ አምላክ ተሰወረብን ማለት አይደለም። ስለዚህ ለስምህ እሰግዳለሁ ስንል፣ ለተጸውዖ ስምህ አደገድጋለሁ ማለታችን አይደለም። ነገር ግን የተጸውዖ ስሙ ባለቤት የህልውናዬ ዐልፋና ዖሜጋ ነው ማለታችን እንጂ። ያህዌ የሚለው ስም ትርጓሜው፣ የእግዚአብሔርን ታዳጊነትና በድነት ውስጥ ያለውን ሉዓላዊ ቦታ

የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ያህዌ ማለት በሁሉ ላይ ሉዓላዊ ሥልጣን ያለው ታዳጊ አምላክ ማለት ነው። ቴትራግራማቶን እንዴት እንደሚነበብ አይታወቅ እንጂ፣ ይህ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ ታዳጊና ልዑል አምላክ እንደ ሆነ የሐዲስ ኪዳን ምንባባትም በዝርዝር ያስረዳሉ። ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔርን ማንነትና የድነት መንገድ እጅግ በተፍታታ መንገድ ገልጸውልናልና።

ስም የሚለውን ቃል በጥሬው በመተርጐም ከመንገድ የሳቱት፣ "የይሖዋ ምስክሮች" ብቻ አይደለሁም። "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"[13] በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት መምህራንም ጭምር እንዲሁም የዘመኑ አባይ ነባዮች እንጂ። "የአንሊ ጂሰስ" መምህራን በዮሐንስ 5÷43 ላይ፣ "እኔ በአባቴ ስም መጥቼ አልተቀበላችሁኝም፤ ሌላው በራሱ ስም ቢመጣ ግን ትቀበሉታላችሁ" የሚለውን አሳብ በመጥቀስ፣ "ኢየሱስ በአባቴ ስም መጣሁ" ሲል "ኢየሱስ ራሱ አብ ሆኖ መምጣቱን"፣ "የኢየሱስ ስም ማለት የአብ ስም መሆኑን"፣ "አብና ወልድ አንድ አካል

[13] በኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት የሚታወቁት "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በሚለው ስማቸው ሲሆን በተለምዶ ግን "ኦንሊ ጂሰስ" በሚለው ስም በስፋት ይታወቃሉ። "ኦንሊ ጂሰስ" የሚለው ስያሜ የመጣው ድርጅቱ የሥላሴን አስተምህሮ በመካድ አብም፣ ወልድም፣ መንፈስ ቅዱስም አንድ አካል ናቸው የሚለውን ትምህርት በማራመዱ ነው። ይህ ትምህርት በኒቂያ ጉባኤ አበው፣ "ውጉዝ ከመሰባልዮስ" ተብሎ ተወግዞአል። "ኦንሊ ጂሰሶች" በምዕራቡ ዓለም በተለያየ ስም ይጠራሉ፤ በአሜሪካን አገር የሰባልዮስን አስተምህሮ በማራመዱና የኢትዮጵያውን "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመቈርቈሩ ምክንያት በስፋት የሚታወቀው፣ "ዩናይትድ ፔንቴኮስታል ቸርች" *(UPCI)* የሚባለው ድርጅት ነው። ይህ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ሁለት ሚሊዮን አባላት እንዳሉት ጥናቶች ያሳያሉ፤ የወቅቱ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴርም የዚሁ ድርጅት አባል እንደ ሆኑ ይነገራል።



መሆናቸውን" ያሳያል ይላሉ። ይህ ፍጹም ስሕተት ነው። በዚሁ ዐውድ ወስጥ ኢየሱስ ራሱ፣ "እኔ ብቻዬን ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም፤ የምፈርደው የምሰማውን ብቻ ነው፤ የላከኝን እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለማልሻም ፍርዴ ትክክል ነው። 'እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር፣ ምስክርነቴ ተቀባይነት አይኖረውም። ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ አለ፤ እርሱ ስለ እኔ የሚሰጠውም ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ ዐውቃለሁ'" (ዮሐንስ 5÷30-32)። ኢየሱስ፣ "ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ አለ" የሚለው አነጋገሩ ምስክር በሁለት ወይም በሦስት ይጸናል የሚለውን የብሉይ ኪዳን ክፍል ታሳቢ ያደረገ ነው (ዘኍልቍ 35÷30፤ 17÷6፤ 19÷15)።

ኢየሱስ ራሱ አብም ወልድም ከሆነ፣ እርሱ ራሱ ስለራሱ መስክሮአልና እርሱ ራሱ እንደ ተናገረው ምስክርነቱ እውነት ሊሆን አይችልም። ነገረ ግን አብና ወልድ የተለያዩ አካላት በመሆናቸው አንዱ የሚመሰክርለት ሌላው ደግሞ የሚመሰክር ሆኖ ቀርቧል። እንዲሁም በዚሁ ዐውድ ውስጥ፣ "ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም"፣ "የምፈርደው የምሰማውን ብቻ ነው"፣ "የላከኝን እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለማልሻ"፣ ወዘተ የሚሉት አነጋገሮች አብና ወልድ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ናቸው—የሚያይ ዐይን ላለው ዐይናማ ማለቱ ነው።

በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ስም የሚለው ቃል 156 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ሁሉ በእነዚህም መጻሕፍት ስም ባሕርይን፣ ግብርንና ሥልጣንን የሚያመለክት ሆኖ ነው የቀረበው። በሌላ አነጋገር "በ__ስም" ማለት "በ__ሥልጣን" ማለት ነው። በዚህ አንጻር አንድ ክፍል እንመልከት፡—

“ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን እንዲህ አለው፤ አንተ ሰይፍ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ ተምጣብኛለህ፤ እኔ ግን አንተ በተገዳደርኸው የእስራኤል ሰራዊት አምላክ በሆነው፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ” *(1ሳሙኤል 17÷45)*፡፡

በዚህ ክፍል ዳዊት፣ “በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ” ሲል፣ ስሜ እግዚአብሔር ተብሎ ወይም እኔና እግዚአብሔር አንድ አካል ሆነን እመጣብሃለሁ ማለቱ ሳይሆን፣ በተገዳደርኸው በእግዚአብሔር ሥልጣን እመጣብሃለሁ ማለቱ ነው፡፡ ልክ እንደዚሁ ሁሉ ኢየሱስ፣ “በአባቴ ስም መጣሁ” ሲል፣ “የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” መምህራን እንደሚያስተምሩት የአብና የወልድ ስም አንድ ነው ወይም አብና ወልድ አንድ አካል ናቸው ለማለት ተፈልጎ ሳይሆን፣ በአባቴ ሥልጣን ወይም አባቴን ወክዬ መጥቻለሁ ማለቱ ነው፡፡

ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ “ይሖዋ ምስክሮች” ያህዌ የሚለውን ስም በጥሬው በመተርጐም፣ ትልቅ የነገረ መለኮት ኪሣራ ውስጥ እንደ ወደቁ ሁሉ፣ “የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” መምህራንም ኢየሱስ የሚለውን የተጸውዖ ስም በተሳሳተ መንገድ በመተርጐም ከእውነተኛው አስተምህሮ ስተው ወጥተዋል፡፡ እነዚህ “የአንስ ጂሰስ መምህራን”፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብቻ መጠመቅ አለባቸው የሚለው ትምህርት የመነጨው በትምህርተ ሥላሴ ላይ ካላቸው መስመር የሳተ አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን፣ በኢየሱስ ስምም ላይ ካላቸው ስሑት ነገረ መለኮት የመነጨ ነው፡፡ የድርጅቱ መምህራን ሰዎች፣ “በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም” መጠመቅ የሰባቸውም የሚለውን ሙግት ያዋቀሩት፣ “አብ፣ ወልድና መንፈስ



ቅዱስ” የሚሉት ስሞች፣ የኢየሱስ የማዕረግ ስሞች ናቸው ከሚለው አስተሳሰብ በመነሣት ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስ በሚለው የተጸውዖ ስም ላይ የተዛባ አመለካከት መያዛቸው ነው፡፡

“ኢየሱስ ክርስቶስ” የሚለው የአማርኛ ስያሜ ከግሪክ አቻው በቀጥታ የተወረሰ ነው፡፡ “ኢየሱስ” (በዕብራይስጥ የሹዋ ישׁוּעַ በግሪክ የሱስ Ἰησοῦς) ማለት “እግዚአብሔር ያድናል” ማለት ሲሆን፣ “ክርስቶስ” (በዕብራይስጥ ማሺያኽ מָשִׁיחַ፣ በግሪክ ክርስቶስ χριστός) ማለት ደግሞ የተቀባ ማለት ነው፡፡

ኢየሱስ የሚለው ስም በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ሰዎች በብዛት ይጠሩበት የነበረ ስም ነበር፡፡ “ኢየሱስ” ለሚለው የግሪክኛና የአማርኛ ስያሜ የዕብራይስጥ አቻው፣ የሹዋ ወይም ኢያሱ የሚለው የተጸውዖ ስም ነው—በድምፀትም በትርጉምም፡፡ ጌታ በተወለደበት በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ከየትኛውም የዕብራይስጥ ስም ይልቅ ኢየሱስ የሚለው ስም የብዙ ሰዎች መጠሪያ እንደ ነበር ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ የፍልስፍናና የነገረ መለኮት ምሁሩ ፕሮፌሰር ጌሪ ሃበርማስ፣ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ከዘጠና ዘጠኝ ስሞች መኻል ሃያ ሁለቱ ኢየሱስ የሚለው ስም እንደ ሆነ በማስረጃ ይሞግታል፡፡ ይህ ማለት ከአምስት ሰዎች መኻል አንዱ፣ ስሙ ኢየሱስ ወይም የሹዋ ነው ማለት ነው[14]፡፡

በፊልጵስዩስ መልእክት ላይ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ከመስቀል ሞቱና ሞትንም ድል አድርጎ ከተነሣ በኋላ፣

---

[14] በሚከተለው ድረ ገጽ ላይ ይህን መረጃ የወሰድነው ወርኀ ጥቅምት 2013 ዓ.ም ላይ ነው፡፡
*www.garyhabermas.com/articles/The_Lost_Tomb_of_Jesus/losttombofjesus_response.htm*

"እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይኸውም በሰማያና በምድር፣ ከምድርም በታች፣ ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው" *(2÷9-11)* የሚል ቃል እናነባለን።

በዚህ ቦታ ኢየሱስ የሚለው ስም፣ ጌታ ወደ መስቀል ከመሄዱ በፊት ይጠራበት የነበረው ስም ነው። ይህ ምንባብ እየተናገረ ያለው ኢየሱስ ስለሚለው የተጸውዖ ስም ሳይሆን፣ ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ በመነሣት ከፍተኛ ክብር እንደ ተጐናጸፈ የሚያሳይ ነው (ኤፌሶን *1÷21*፤ ዕብራውያን *1÷4-5*)። ምክንያቱም ኢየሱስ የሚለው ስም ቀድሞውኑ ይጠራበት የነበረ ስም ነውና። ንጉሥ ዳዊት፣ "አቤቱ ስለዚህ በአሕዛብ ዘንድ አመሰግንሃለሁ፤ ለስምህም እዘምራለሁ" (መዝሙር *18÷49*) እንዲሁም "ለእግዚአብሔር ተቀኙ፤ ለስሙም ዘምሩ፤ ወደ ምድረ በዳ ለወጣም መንገድ አድርጉ፤ ስሙ እግዚአብሔር ነው" (መዝሙር *68÷4*) ሲል፣ አምላክ ለሚጠራበት የተጸውዖ ስም አዘምራለሁ ማለቱ እንዳልሆነ ሁሉ፣ ጉልበት ሁሉ የሚንበረከክለት ስም የኢየሱስ ስም ነው ማለት የተጸውዖ ስሙ፣ ከኢየሱስ በተለየ መልኩ ስግደት ይቀርብለታል ማለት አይደለም።

ከላይ በስፋት ለመመልከት እንደ ሞከርነው ስም፣ የስሙ ባለቤት ያለውን ባሕርይ፣ ግብርና ሥልጣን የሚያመለክት ስያሜ ነው። ስለዚህ በክርስቶስ ስም ተሰብሰቡ ማለት በምትሰበሰቡበት ጊዜ በኢየሱስ ስም በሉ ማለት ሳይሆን፣ በእርሱ ሥልጣን ሥር ስብሰባችሁን አካሂዱ ማለት ነው (ማቴዎስ *18÷20*፤ *1*ቆሮንቶስ *5÷4*)።



ድነትን ወይም ንስሓና የኀጢአት ይቅርታን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስበኩ ማለት፣ ኢየሱስ ለሰዎች ድነት ያደረገውን ገድል ተርኩ ወይም ሞትና ትንሣኤውን ስበኩ ማለት ነው (ሉቃስ *24÷47*፤ ሐዋርያት ሥራ *4÷12*፤ ዮሐንስ *1÷12*፤ ሐዋርያት ሥራ *10÷43*፤ *1*ዮሐንስ *3÷23*፤ *5÷13*)። በአጭሩ ስም የስሙ ባለቤት ካለው ባሕርይ፣ ግብርና ሥልጣን የተለየ ፋይዳ ያለው ነገር አይደለም።

እንግዲያው እውነቱ ይህ ከሆነ፣ በጸሎታችን ማጠናቀቂያ ላይ፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ብለን ጸሎታችንን ማሳረግ የለብንም ማለት ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ተገቢ ጥያቄ ነው።

"በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" መጸለይ ማለት፣ እንደ ክርስቶስ አስተምህሮና እንደ እርሱ ፈቃድ በመጸለይ የእርሱን ክብር መሻት እንደ ሆነ ከላይ ለማየት ሞክረናል፤ "ማንኛውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን እርሱ ይሰማናል" *(1ዮሐንስ 5÷14)*። ስለዚህ አንድን ጸሎት ክርስቲያናዊ ጸሎት የሚያሰኘው በጸሎቱ መቋጫ ላይ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ማለታችን ሳይሆን፣ ከጸሎቱ ጅማሬ እስከ ጸሎቱ ፍጻሜ የክርስቶስን አሳብ የሚወክልና የእርሱን ክብር የሚሻ መሆን ይኖርበታል። መጽሐፍ ቅዱስ በኢየሱስ ስም ጸልዩ ሲለን፣ ቀዳማይ መልእክቱ ይኸው ነው። ይዘቱ እርሱን የሚያስከብር ከሆነ፣ በጸሎቱ ማጠናቀቂያ ላይ "በኢየሱስ ስም" ማለታችን እንዳችም ክፋት የለውም—ለእርሱ ያለንን አክብሮት የሚያሳይ እስከ ሆነ ድረስ አግባብ ነው።

"በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ብለን አጋንንትን ማውጣት የለብንም ማለት ነው? ይህም ሊጠየቅ የሚገባው ተገቢ ጥያቄ ነው። ይህን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ አንድ ሁነኛ የሆነ ጥያቄን ገፋ አድርገን እንመርምር። ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጸውዖ

ስምና (ለምሳሌ ሙሴ፣ ማርያም፣ ኢየሱስ፣ ገብርኤል፣ ያህዌ)፣ በማዕረግ ስም[15] (መቶ አለቃ፣ ጌታ፣ ንጉሥ፣ እግዚአብሔር ወዘተ) መካከል፣ የስዋስው ስያሜ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር፣ አንዳችም የፅንስ ሐሳብ (የይዘት) ልዩነት ያለመኖሩን ነው። ዘመነኞቹ የሰዋስው ምሁራን ስሞችን በተለያየ ፈርጅ መድበዋቸዋል። ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ግን አጠቃቀማቸውን በተመለከተ በተጸውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም ልዩነት አላደረጉም። በዚህ ረገድ አንዳንድ አስረጆችን እንመልከት:— *(1)* ክላይ ለማየት እንደ ሞከርነው ያህዌ የሚለው የተጸውዖ ስም፣ በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትና በሰብዐ ሊቃናት ትርጉሞች ላይ፣ አምላክና እግዚአብሔር በሚሉ የወል ስሞች ተተክቶአል–አንዳችም የትርጉም ልዩነት ሳይኖራቸው። *(2)* ብሉያትም ሆኑ ሐዲሳት በተጸውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም ልዩነት አላበጁም። በዚህ ረገድ የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል:—

- ○ "ቀናተኛ" የሚለው ስም የእግዚአብሔር "ስም" እንደ ሆነ ተገልጾአል (ዘፀአት *34÷14*)።
- ○ "ድንቅ መካር"፣ "ኃያል አምላክ"፣ "የዘላለም አባት"፣ "የሰላም አለቃ"፣ የሚሉት ቅጽሎች የመሲሑ "ስም" ናቸው ተብሏል (ኢሳይያስ *9÷6*)።
- ○ "ቅዱስ" የሚለው ቅጽል የእግዚአብሔር "ስም" እንደ ሆነ ተነግሮናል (ኢሳይያስ *57÷15*)።

[15] ብላታ መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ *የአማርኛ ሰዋስው* በሚለው መጽሐፋቸው፣ እኔ የማዕረግ ስም ያልሁትን፣ እርሳቸው የወል ስምና የጥቅል ስም በሚለው ጉራ ውስጥ ፈርጀውታል፤ ገጽ *17-22* ይመለከቷል።



- ○ "አዳኝ" የሚለው "ስም" ነው (ኢሳይያስ *63÷16*)።
- ○ "ክርስቶስ" "ስም" ነው (ማቴዎስ *24÷5* ከ*1*ጴጥሮስ *4÷14* ጋር ያነጻጽሯል)።
- ○ "የእግዚአብሔር ቃል" "ስም" ነው (ራእይ *19÷13*)።
- ○ "የነገሥታት ንጉሥ"፣ "የጌቶች ጌታ" ስም ነው (ራእይ *19÷13*)።

"አምላክ"፣ "ጌታ" እና "እግዚአብሔር" በሚሉት ስሞች ላይ "የእኛ" ("የእኛ አምላክ")፣ "የእስራኤል" ("የእስራኤል አምላክ") ወዘተ የሚሉት ቅጽሎች ተቀጽለውበት የሚገኝ ስለሆነ፣ ቃሉ የማዕረግ ስምን ማሳየቱ እሙን ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ይህ ዐይነቱ የማዕረግ ስም የተጸውዖ ስም ሆኖ ሲያገለግል እንመለከታለን። በዕብራይስጥ "መሲሕ" (ማሻኽ)፣ በግሪክ "ክርስቶስ" የሚለው ቃል፣ የማዕረግ ስምን በሚያሳይ መልኩ ጥቅም ላይ ውሎአል (ለምሳሌ ማቴዎስ *16÷16*፤ ሉቃስ *24÷46*፤ ዮሐንስ *1÷41*)። በአንጻሩ ደግሞ "ክርስቶስ" የሚለው ይኸው ቃል፣ የተጸውዖ ስምን በሚያመለክት መልኩ በአብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ አገልግሎአል ("ኢየሱስ ክርስቶስ" እንዲሉ)። ክዚህ የምንማረው ትልቁ ቁም ነገር፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በተጸውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል አንዳችም የትርጉም/የፅንሰ ሐሳብ ልዩነት ያለማድረጋቸውን ነው።

"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" መምህራን ("ኦንሊ ጂሰሶች") በተጸውዖ ስምና በማዕረግ ስም መካከል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ልዩነት በማኖራቸው ምክንያት፣ ማቴዎስ *28÷19* ላይ የምናገኘውን፣ "አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን የጥምቀት ቀመር፣ ስሞችን በማጥመቅ ሂደት ውስጥ ተፈጻሚ ልናደርገው አንችልም

ባይ ናቸው። ስዚህ ምክንያታቸው ደግሞ፣ "አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ" የሚሉት ቃላት የተጸውዖ ስም ሳይሆኑ፣ የማዕረግ ስም ናቸው፤ በማዕረግ ስም ደግሞ ማጥመቅ በትክክል፣ እግዚአብሔርን እያመስከትም (በግእዝ ቋንቋ "አብ" ስንል "አባት" ማለታችን፣ "ወልድ" ደግሞ ስንል "ልጅ" ማስታችን ነውና። ብዙ አባቶች ብዙ ልጆች ባሉበት ምድር በዚህ ዐይነት መልኩ ጥምቀትን ማካሄድ ስሕተት ነው) ባዮች ናቸው[16]።

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን፣ በተጸውዖ ስምና በማዕረግ (በወል) ስም መካከል አንዳችም የይዘት ልዩነት እንደ ሌስ ክላይ ተመልክተናል፤ ይህ አንደኛውና መሠረታዊው ነጥብ ነው። ሁስተኛው ነጥብ፣ በማቴዎስ 28÷19 ጌታ፣ "በአብ፣ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም" አጥምቁ ብሉናል። እነርሉ እንደሚሉት በማዕረግ ስምና በተጸውዖ ስም መካከል የይዘት ልዩነት ቢኖር ኖሮ፣ ጌታ በማዕረግ *ስም አጥምቁ* የሚል ትእዛዝ አይስጠንም ነበር[17]።

በአጠቃላይ በማዕረግ ስምና በተጸውዖ ስም መካከል ያሰው ልዩነት የሰዋስው ስያሜ ልዩነት እንጂ፣ የፅንስ ሐሳብ (የትርጉም) ልዩነት እንዳልሆነ በግልጽ መረዳት ይኖርብናል። ስለዚህ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቃችን ወይም ማጥመቃችን፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ሥር ማደራችንን የሚያሳይ ነው።

---

[16] ተክለ ማርያም ገዛኸኝ፤ *እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል አዲስ ልደት!* (አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ) ገጽ 117።

[17] *ይህ መናፍቃዊ ድርጅት በጥምቀት ላይ የሚያስተምረውን የተሳሳተ ትምህርት በስፋት ለመመርመር ከፈለጉ፣ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ፣ ሰባልዮሳውያን በሚል ርእስ ያዘጋጃቸውን ሁለት ተከታታይ ቅጽ መጻሕፍት ይመለከቷል።*



ስለዚህ ስይጣንን "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም" ብቻ ሳይሆን፣ "በወልድ ስም"፣ "ድንቅ መካር፣ ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የስላም አለቃ ስም"፣ "በአዳኙ ስም"፣ "በክርስቶስ ስም" ወዘተ ብለን በመቃወም ማባረራችን አግባብ ነው። እነዚህ ስሞች ሁሉ የሚያመለክቱት ያው አንዱን ክርስቶስ፣ አንዱን ጌታ ነውና።

እነዚህ ሁሉ ስሞች የኢየሱስ ስሞች እንደ ሆኑ የነገሩን ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ይጠራባቸው ዘንድ እርሱን ስለሚመጥኑት፣ ባሕርዩንም ስለሚያመለክቱ ነው። "መቶ አለቃ" የሆነን ወታደር፣ "ሃምሳ አለቃ" ወይም "ሻለቃ" ወይም ደግሞ "ኮሎኔል" ብሎ መጥራት ስሕተት ነው። ሃምሳ አለቃ የሚለው ማዕረግ የግለሰቡን ሥልጣን የሚያሳንስ ሲሆን፣ ሻለቃ ወይም ኮሎኔል ብሎ መጥራት ከግለሰቡ ሥልጣን በላይ ስለሆነ ስሕተት ነው። ኢየሱስ በተለያዩ ስሞች የተጠራው ስሞቹ ሁሉ በትክክል እርሱን ስለሚመጥኑት ነው። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ፣ አንዱን የጌታ ስም ከሌላው ስም ማበላለጥ ትክክል አይደለም።

ዳዊት ጐልያድን፣ "ዳዊትም ፍልስጥኤማዊውን እንዲህ አለው፤ አንተ ሰይፍ፣ ጦርና ጭሬ ይዘህ ትመጣብኛለህ፤ እኔ ግን አንተ በተገዳደርኸው የእስራኤል ሰራዊት አምላክ በሆነው፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር ስም እመጣብሃለሁ" (1ሳሙኤል 17÷45) ሲለው፣ ዳዊት የውክልና ጦርነት እንደሚዋጋ የሚያሳይ እንጂ፣ ወንጭፉን ባስወነጨፈ ጊዜ ሁሉ የአምላክን ስም መጥራቱን የሚያመለክት አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መልእክት ይህ ሆኖ ሳለ፣ የያህዌን ስም (የኤልሻዳይን ወዘተ ስም) ጠርቶ ወንጭፉን ቢያስወነጭፍ ደግሞ አንዳችም ስሕተት ያለበትም፤ ሊኖርበትም አይችልም። ስለዚህ የክርስቶስን ስም እየጠራን

አጋንንትን ማስወጣት እንችላለን፤ ነገር ግን የጌታን ስም ጥሩ የሚለውን ቃል ከመሠረታዊ ትርጒሙና መጽሐፍ ቅዱስ ሊያስተላልፈው ከሚፈልገው ትምህርት በወጣ መልክ ልንረዳው አይገባም።

መጽሐፍ ቅዱስ "በስሜ አጋንንትን" እውጡ ሲለን[18]፣ የዚህ ዓለም ገዢ በሆነው በዲያብሎስና በጭፍሮቹ ፊት ክርስቶስን ወክላችሁ ቅረቡ ማለት ነው—ከላይ ባየነው ክፍል ዳዊት፣ ያህዌን ወክሎ በጎልያድ ፊት እንደ ቀረበው ማለት ነው። "የኢየሱስን ስም" መጥራት ብቻ በራሱ ተኣምር የሚያደርግ ቢሆን ኖሮ፣ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ያልተቀበሉ አይሁድ፣ የኢየሱስን ስም በመጥራት አጋንንትን ለማውጣት ያደረጉት ሙከራ አይከሽፍም ነበር። እንዲያውም ይህን ለማድረግ ሙከራ ባደረጉት ሰዎች ላይ እርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ክፉኛ እንዳጠቃቸው ከዚህም የተነሣ፣ የነበሩበትን ቤት ዕርቃናቸውን ጥለው እንደፈረጠጡ እንመለከታለን። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ፣ "ኢየሱስ" የሚለውን የተጸውዖ ስም መጥራት ሳይሆን፣ በዚህ ስም የሚጠራውን ታላቅ ጌታ በእምነት ወክሎ የመቅረቡ ጒዳይ፣ ዋነኛ ነገር እንደ ሆነ የሚያሳስብ ነው።

"እየዞሩ አጋንንትን ያስወጡ ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶቹ፣ 'ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ ስም እንድትወጡ እዛችኋለሁ!' እያሉ የጌታን የኢየሱስን ስም ርኩሳን

[18] መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ" (ማርቆስ 16÷17) የሚለውን ክፍል፣ "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጋንንትን ያወጣሉ" ብለን ልናነበው አይገባም። ስለዚህ የኢየሱስ የሆኑ ስሞችን ሁሉ እርሱን የሚመጥኑት ከሆነ፣ እነዚህን ስሞች ሁሉ በመጥራት አጋንንትን ብናወጣ ተሳስታችኋል ልንባል አንችልም።



መናፍስት በያዟቸው ሰዎች ላይ ለመጥራት ሞከሩ፤ የአይሁዳዊው የካህናት አለቃ የእስቄዋ ሰባት ወንዶች ልጆችም ይህንኑ ያደርጉ ነበር። ርኩስ መንፈሱም፣ 'ኢየሱስን ዐውቀዋለሁ፤ ጳውሎስንም ዐውቀዋለሁ፤ እናንተ ግን እነማን ናችሁ?' አላቸው። ከዚያም ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ዘሎ ያዛቸው፤ በረታባቸውም፤ እጅግ ስላየለባቸውም ቤቱን ጥለው ዕራቍታቸውን ሸሹ" (ሐዋርያት ሥራ 19÷13-16)።

## ማጠቃለያ

በዚህ ክፍል ቅዱሳት መጻሕፍት የአምላክን የተጸውዖ ስም በተመለከተ ያላቸውን ትምህርት ለመዳሰስ ሞክረናል—በተለይ ክርኣሰ ጒዳዩ ጋር በተገናኘ፣ ትልቅ የእስተምህሮ አደጋ ሲጋርጡ የሚችሉትን አንኳር አንኳር መሰናክሎች ከመንገድ ላይ ገለል ያደረግናቸው ይመስለኛል። በቅዱሳት መጻሕፍት ስም ባሕርይን፣ ግብርንና ሥልጣንን የሚያመለከት ሁነኛ ሰነደቅ ዐላማ ነው።

የአንድ ተጸውዖ ስም ታላቅነት የሚወሰነው፣ የስሙ ባለቤት ማን ነው በሚለው ማመሳከሪያ እንደ ሆነ ሁሉ የአምላክ ስም ታላቅ፣ ክቡር…የሆነው አግዚአብሔር እምላካችን ክቡርም ትልቅም ስለሆነ ነው። "የያህዌን ስም ከፍ ማድረግ" ማለት፣ እግዚአብሔርን በኑሮአችንና በአገልግሎታችን የበላይ ማድረግ ማለት አንጂ፣ እምላከን በተጸውዖ ስሙ መጥራት ማለት አይደለም።

"በክርስቶስ ስም መጸለይ" ማለት በጸሎት ማጠናቀቂያ ላይ "በኢየሱስ ስም" ማለት ሳይሆን፣ አንደ ክርስቶስ አሳብና ፈቃድ ጸሎትን ማድረስ ማለት ነው። በክርስቶስ ስም መሰብሰብ፣ ለክርስቶስ

ስም መስገድ ወዘተረፈ ማለት፣ በእርሱ ሥልጣን ሥር መዋቀር፣ በእርሱ ማዕከልነት መደራጀት፣ በእርሱ ጥላ ሥር መጠለል፣ በመጠጊያነቱ ውስጥ ማደር፣ ለእርሱ አምልኮተ ስግደት ማቅረብ፣ እንደ ቃሉ መኖር ወዘተ ማለት ነው። እንግዲያው የእግዚአብሔርን ስም የምንቀድሰው፣ ኑሮአችንንና አስተሳሰባችንን በእርሱ አሳብና ፈቃድ ውስጥ በመክተት እንጂ፣ በአንድ ግብር መጨረሻ ላይ የተጸውዖ ስሙን በመጥራት ወይም ባለመጥራት አይደለም።

አባይ ነባዮች ያሻቸውን አድርገው፣ በድርጊታቸውም መጨረሻ "በኢየሱስ ስም" ማለታቸው፣ ግብራቸውን አያጸድቅም አስተምህሮአቸውን ርቱዕ አያደርገውም። "ኢየሱስ" የሚለው ስም መጠሪያ እንጂ፣ ምትሐታዊ ቀመር አይደለምና።

እንዲያውም መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን አባይ ነባዮች "እኔ ኢየሱስ ነኝ" እያሉ በስሙ እንደሚመጡ ጌታ ራሱ ነግሮናል፣ "ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፣ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ…ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፤ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ" (ማቴ. 24፥4-5፡24)። ወገን ስማ—የኢየሱስን ስም የጠራ አባይ ነባይ ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር ነው ማለት ስሕተት ነው።



# ክፍል ዐሥራ አንድ

## የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን መበራከት ምስጢር ምንድን ነው?



### ሀ. ሰዎች አባይ ነባዮችን እንዲሁም መናፍቃንን ለምን ይከተላሉ?[1]

### አጠቃላይ አሰሳ

የአንድን ክሥተት ትክክለኛ መንሥኤ ማወቅ፣ የመፍትሔው አስተንትኖት ቀዳማይ እርምጃ ነው።

[1] የክፍሉ ጭብጥ በአብዛኛው የተወሰደው፣ ከሚከተለው መጽሐፍ ነው፡— Alan W. Gomes, *Unmasking the Cults* (Grand Rapids: Zondervan, 1995), 81-85.